




አቡነ ተክለሃይማኖት

ቅዱስ ጊዮርጊስ

# ትንሣኤ



ዋጋው ፬ ሣንቲም

ቁጥር ፴፱

ነሐሴ ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

www.ethiopianorthodox.org

"ይህ መጽሔት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ሥርዓትና ዜና ፣ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጭምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ።"


አዘጋጅ
ራደ አስረስ



በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ
ሐዋርያዊ ድርጅት
የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ
በወር አንድ ጊዜ
እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 116616
የመልእክት ሣ.ቁ. 3137
አዲስ አበባ


ማውጫ


| አርእስት | ገጽ |
| --- | --- |
| ድንግል ማርያም የሴቶች መመኪያ | ፫ |
| የምሥጢር ሰዎች | ፬ |
| ጎብስት ስርጉባን | ፮ |
| ክቡር ሞቱ ለጻድቅ | ፯ |
| ቤተ ክርስቲያንና ንብረተ ሰብእ | ፰ |
| የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ | ፱ |
| ቅዱስ ሩፋኤል | ፲ |
| የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት | ፲፪ |
| ትምህርተ ግእዝ | ፲፬ |
| ወጣቶች በጾመ ፍልሰታ | ፲፮ |
| ደብዳቤዎች | ፲፯ |
| ከሕግ ለወጡ ሰላም የላቸውም | ፲፯ |
| ዜና ሊቃውንት | ፲፱ |
| ከቤተ ክርስቲያን የታሪክ ማህደር | ፳ |
| ልማት በቤተ ክርስቲያን | ፳፩ |
| የቤተ ሰብእ ዓምድ | ፳፫ |




የብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክና የቅዱስ ሲኖዶስ ሊቀመንበር ፭ኛ ዓመት በዓለ ሢመት በጸሎትና በታላቅ መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ነሐሴ ፳፫ ቀን ፲፱፻፹፰ ዓ.ም. በመንበረ ፓትርያርክ ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ይከበራል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ድንግል ማርያም የሴቶች መመኪያ

እግዚአብሔር ሰውን ሲፈጥር ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠረ እንጂ የወንዶችን መብት ከሴቶች መብት አላበለጠም ፣ የሴቶችንም መብት ከወንዶች አላሳነሰም ። በኋላ ግን ሰው በምድር ላይ መኖሩን ሲቀጥል የራሱን ክብር ከፍ የሌላውን ዝቅ ማድረግ ጀመረ ፣ ሀብት ያለው የድሃውን ጉልበት ያለው የደካማውን መብት እየገፈፈ ባመጣው የኑሮ ውጣ ውረድ ወንዶችም የሴቶችን መብት ዝቅ የራሳቸውን መብት ከፍ ማድረግ እንደጀመሩ የታሪክ ሊቃውንት ያትታሉ ።

በሃይማኖት ትምህርትም የመጀመሪያው ሰው አዳም በሔዋን እጅ ዕፀበለስን በልቶ ከገነት በመውጣቱና ከእግዚአብሔር በመለየቱ የአዳም ልጆች ሁሉ ወንዶቹ ሴቶቹን በሔዋን ምክንያት ከገነት ወጣን ፣ ከእግዚአብሔር ተለየን በመንጸፈ ደይን ወደቅን በጠላታችን በሰይጣን እግር ተረገጥን ። እያሉ ይመፃደቁባቸው ነበር ። በዚህም ምክንያት ሴቶችን ዝቅ ራሳቸውን ከፍ እያደረጉ እኩልነታቸውን አሳጡአቸው ። ሴቶች ሁሉ በዚህ ምክንያት እያዘኑ ለእኩልነታቸው እየተቆረቆሩ ዘመናትን አሳለፉ ።

በኋላ ግን የሰዎች በሰዎች መገፋትና በሰይጣን አገዛዝ ሥር መውደቅ እግዚአብሔርን አሳዘነው ። ስለሆነም አንድ ልጁን እግዚአብሔር ወልድን ወደ ዓለም ላከው እግዚአብሔር ዓለሙን የሚታረቅበት በስሙ የሚያምኑትን ከሰይጣን አገዛዝ ነፃ የሚያወጣበትና ሁሉን በእኩልነት ወደ እርሱ የሚያቀርብበት ጊዜ ሲደርስ እግዚአብሔር ወልድ ከድንግል ማርያም ያለአባት በሥጋ ተወለደ ገላ.4.4።

ያለ ሩካቤ በኅቱም ድንግልና ተጸንሶ በኅቱም ድንግልና የተወለደው እግዚአብሔር ወልድ የአዳምንና የሔዋንን በደል በሥጋው በመስቀል ላይ በተሸከመና ደሙን ባፈሰሰ ጊዜ ሔዋን ዕፀበለስን በመብላቷ ምክንያት የተዘጋው የገነት በር ድንግል ማርያም ክርስቶስን በድንግልና በመውለድዋና ከእርስዋ በተዋሐደው ሥጋ በመሰቀሉ ተከፈተ ። ስለዚህም የሶርያው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም "በሔዋን ምክንያት የገነት በር ተዘጋ ዳግመኛም በድንግል ማርያም ምክንያት ተከፈተልን ።" በማለት ተናግርአል ኤፍሬም ፬.፪ ።

እንዲሁም በጥንተ ተፈጥሮ ሔዋን ከአዳም በመገኘቷ ምክንያት ሴት ከወንድ ተገኘታለች እንጂ ወንድ ከሴት አልተገኘም እያሉ ወንዶች በሴቶች ይመኩባቸውና የበላይነት ያሳዩባቸው ነበር ።

• መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ አባት ከድንግል ማርያም ከተወለደ በኋላ ግን ሔዋን ያለ እናት ከአዳም ብትገኝ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያለ አባት ከድንግል ማርያም ተወልዶ የለምን በማለት ሴቶች መንፈሳዊ መብታቸውን ለማሳወቅ በቅተዋል ይህም የሴቶች መብት በእመቤታችን እንደተረጋገጠ ለማስረዳት ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ " ለወንዶች የሚከፈለው ዕዳ በሴቶች ላይ ነበረ ። ሔዋን ያለ እናት ከአዳም ተገኘታ ነበርና ስለዚህም ድንግል ያለ ዘርአ ብእሲ ክርስቶስን ወለደች ። የሔዋንን ብድራት ለአዳም ትከፍለው ዘንድ አዳም ያለ እናት ሔዋንን ስለ አስገኘ እንዳይመካ ድንግል ያለ አባት ክርስቶስን ወለደች ይኸውም ድንቅ በሚሆን አንድነት ይህ አንድ የፍጥረት እኩልነት ይታወቅ ዘንድ ነው ።"(ሃይ አ በ ም. ፷፯ ክ.፴ ቁ.፳፱) በማለት ድንግል ማርያም ለሴቶች መብት መመኪያቸው እንደሆነች አስተምርአል ።

ይህንና የመሳሰለውን የተፈጥሮ ሕግና የክርስትና ትምህርት የተረዱ ወገኖች በሴቶች መብት ያምናሉ ። በሔዋን (በሴት) ምክንያት ሞት ወደ ዓለም እንደመጣ የሚያምኑ በድንግል ማርያም ምክንያት ድኅነት ወደ ዓለም እንደ ገባ ይረዳሉ ፣ በሔዋን ስህተት የተዘጋው የገነት በር በድንግል ማርያም ምክንያት ተከፈተ ሔዋን ዕፀ በለስን በልታ ምክንያተ ሞት ቃየልን ወለደች ድንግል ማርያም ግን የመልአኩን ብሥራት ሰምታ የሕይወት ራስ ክርስቶስን በድንግልና ወለደች ። በሔዋን ምክንያት በሰዎች ላይ የነበረው መርገም ከድንግል ማርያም በተወለደው በክርስቶስ ተወገደ ። ወንዶች በሴቶች ላይ ያሳዩት የነበረው ተግዳሮት ተቃለለ የሴቶች መብት ታወቀ

ስለዚህ ድንግል ማርያም የክርስቲያኖች ሁሉ መመኪያ የድኅነታቸው መሠረት ስትሆን በተለይ ለሴቶች የመብትና የነፃነት መመኪያቸውና መገበኛቸው ናት ስለሆነም "ዳግመኛ በእናትህ ማርያም ተግዕነናል ይህችውም አንተን በመውለድ እመቤታችንና የባሕርያችን መመኪያ ናት ።" እያሉ በእርስዋ ይማጸናሉ ወደ ፈጣሪያቸውም ይጸልያሉ ።



www.ethiopianorthodox.org

# የምሥጢር ሰዎች

ምሥጢር ለሁሉ አይገለጥም ሁሉም ሰው ለምሥጢር አይበቃም ። ምሥጢርም ማለት የማይታይ ረቂቅ ግን የሚታመንና የሚጠበቅ ማለት ነው ። በዚሁም አንጻር የምሥጢር ሰዎች ማለት የተመረጡ ለምሥጢር የበቁ በምሥጢር ያዩትንና የሰሙትን የሚጠብቁ ታማኞች ማለት ነው ።

በመለኮታዊ ምሥጢሩ ሰው የሆነው ወልደ እግዚአብሔር የወንጌል ማስተማር ሥራውን በጀመረ በ፪ ዓመት ከስድስት ወር ይህም ማለት በፈቃዱ ስለእኛ ከመሞቱ ከስድስት ወር አስቀድሞ ሦስቱን ደቀመዛሙርት ጴጥሮስን ያዕቆብንና ዮሐንስን አስከትሎ ወደ ረዥም ተራራ ወጣ ። ተራራው በትምህርተ ሐዋርያት እንደተረጋገጠ ደብረ ታቦር ነው ። ይህም ተራራ በናዝሬት አጠገብ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ ፭፻፰ ሜትር ከባሕር ጠለል በላይ ከፍታ ያለው ተራራ ነው ። በዚህ ተራራ መድኃኒታችንና ጌታቻን ኢየሱስ ክርስቶስ ምሥጢረ መለኮቱን ለሦስቱ ሐዋርያትና ለሁለቱ ነቢያት ለሙሴና ኤልያስ ገለጠ ።

የአገላለጡንም ሁኔታ ኅቡራን (ሲኖፕቲክ) ሦስቱ ወንጌላውያን ማቴዎስ ማርቆስና ሉቃስ ሲያስረዱ እንዲህ ይላሉ ።

"ከስድስት ቀን በኋላ ጌታችን ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ዮሐንስንም ይዞ ወደ ረዥም ተራራ ወጣ ። በፊታቸውም ተለወጠ ልብሱ አንፀባረቀ በጣም ነጭ ሆነ ኤልያስና ሙሴም በክብር ታዩ .... ደመናም መጥቶ ጋረዳቸው ከደመናውም የምወደው ልጄ ይህ ነው ። እርሱን ስሙት የሚል ድምፅ መጣ" (ማር. ፱.፪-፰)

ይህን ሁሉ ምሥጢር ያዩና የሰሙ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ብቻ ናቸው ሌሎች ዘጠኙ ደቀ መዛሙርት ግን ለዚህ ምሥጢር ተካፋዮች እንዲሆኑ ወደ ተራራው አልተጠሩም ይህ ስለሆነም ሦስቱ ደቀ መዛሙርት ከዘጠኙ አይበልጡም ዘጠኙም ከሦስቱ አያንሱም ። ሁሉም በክርስቶስ የተጠሩ ቅዱሳን ሐዋርያት ናቸውና ። ነገር ግን ሐዋርያት ሁሉ የተለያየ ተልእኮ ነበራቸው ። ይህንም በወንጌልና በሐዋርያት ሥራ እንደተጻፈ መረዳት ይቻላል ።

በዚህ መሠረት ጴጥሮስ ያዕቆብና ዮሐንስ በሐዲስ ኪዳን የምሥጢር ሰዎች ነበሩ ። ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ የኢያኢሮስን ልጅ ከሞት በአስነሣ ጊዜ በጌቴሴማኒም በጸለየ ጊዜ እነዚህ ሦስቱ ብቻ አብረውት ነበሩ ።

በብሉይ ኪዳንም ሙሴና ኤልያስ የምሥጢር ሰዎች እንደነበሩ ተገልጦአል ። እግዚአብሔር በደብረሲና ሙሴን ሲያነጋግር እስራኤላውያንን ሁሉ አላነጋገረም ። በዚህም ምክንያት በሙሴ ቀኑ እግዚአብሔርም እንዲያነጋግራቸው ፈለጉ እግዚአብሔርም ሊያነጋግራቸው ሲጀምር ደነገጡና "እግዚአብሔር አይነጋገረን ነገር ግን ሙሴ ያነጋግረን" ብለዋል (ዘዳግ.፭.፳፯) ።

ነቢዩ ኤልያስም እንደ ሙሴ በተመሳሳይ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ድምፅ በደብረ ኮሬብ በዐውሎ ነፋስና በነበልባለ እሳት መካከል ሰምቶአል ። (፩ ነገሥ ፲፱.፯-፲፩) በጠቅላላ የኤልያስ ሕይወት በመለኮታዊ ምሥጢር የተጠበቀ ነው ። ስለዚህ ኤልያስ የምሥጢር ሰው ነው ለማለት ይቻላል ።

ሦስቱ ደቀ መዛሙርት በደብረ ታቦር ያዩት ምሥጢር ምንድን ነው ? ጌታችን ኢየሱስ አምላክም ሰውም ሲሆን ዘወትር በሰብአዊ መልክ ለሰዎች ሁሉ ይታይ ነበር በደብረ ታቦር ላይ ግን ምንም እንኳ ስብሐተ (ክብረ) መለኮቱን አይቶ በሕይወት የሚኖር ባይኖርም እርሱ በፈቀደው መጠን ክብረ መለኮቱን ገለጠላቸው ። ማየት ተስኖአቸው እስከሚወድቁ ድረስ ብርሃነ መለኮቱ በራላቸው ። የእግዚአብሔር አብን ድምፅ ሰሙ ። ክርስቶስ የአብ የባሕርይ ልጅ መሆኑን ከእግዚአብሔር አብ ድምፅ ሰምተው አረጋገጡ ። ሰው ከሞተ በኋላ እንደሚነሣ እስከሚነሣም እግዚአብሔር በፈቀደለት ቦታ በሕይወት እንደሚኖር ሙሴን አይተው ተረዱ ኤልያስንም አይተው እግዚአብሔር የወደዳቸውን በሕይወት ሊያኖራቸው እንደሚችል አስተዋሉ ።

በደብረ ታቦር ያዩትና የሰሙት ምሥጢር ይህ ነው ። የምሥጢር ሰዎችም ያሰኛቸው ይህ ነው ።

አዎ ምሥጢር የሆነው ሁሉ መጠበቅ አለበት ስለዚህም መድኃኒታችን ክርስቶስ ሦስቱ ደቀ መዛሙርት በደብረ ታቦር ያዩት ምሥጢረ መንግሥት በጊዜው እስኪፈጸም ድረስ ለማንም እንዳይናገሩ አዘዛቸው ። ይህም በትንሣኤው እስኪገለጥ ማለት ነው ። ምሥጢረ ደብረ ታቦር ምሥጢረ ትንሣኤን ያመለክታልና ለምሳሌ በደብረ ታቦር ብርሃነ መለኮቱ እንደታየ ልብሱ ፀዓዳ እንደሆነ ሁለት ሰዎች በክብር እንደታዩ ሁሉ በትንሣኤው ዕለትም ይህ ሁሉ ድርጊት ተፈጽሟል ። ብርሃነ ትንሣኤው ተገልጦአል ። ሁለት መላእክት በጸዓዳ ልብስ ታይተዋል ።

ይህ ምሥጢር በደብረ ታቦር ለ፫ ደቀ መዛሙርት የተገለጠበትን ዕለት ክርስቲያኖች ሁሉ በየዓመቱ ያከብሩታል ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክርስቲያንም በየዓመቱ ነሐሴ ፲፫ ቀን በመንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ታከብረዋለች ። ይልቁንም በትውፊታዊው ትምህርት ቤት የሚገኙ ደቀ መዛሙርት ምሥጢር እንዲገለጥላቸው የምሥጢርም ሰዎች እንዲሆኑ በበለጠ ሁኔታ ያከብሩታል ። ሕዝቡም በተራራው ላይ የታየውን ብርሃን መለኮት ለማስታወስ ችቦ ያበራሉ ። ዕለቱም "ቡሄ" በመባል ተለይቶ ይጠራል ። ይህም ብርሃን ማለት ይመስላል ።

ለማጠቃለል ያህል ዛሬም ጌታችን ኢየሱስ ራሱን ሊገልጥ ይፈቅዳል ። ደብረታቦር ብቻ ሳይሆን ሁሉም ቦታ የክብሩ መገለጫ ነው ።

በዚህ አንፃር ዛሬ ሰዎች ሁሉ የምሥጢር ሰዎች እንዲሆኑ ምሥጢረ ወንጌሉን እንዲያስተምሩ የወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ፈቃድ ነው ። " የዚህ ምሥጢር ክብር ... ምን እንደሆነ ሊያስታውቅ (ራሱ ክርስቶስ) መጥቷልና ።

ሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ



# ኅብስት ለርኁባን

በዓለም ውስጥ አሰቃቂዎችና በሰው ላይ ከፍተኛ ችግርን ያደርሳሉ ተብለው ከሚፈሩ አደገኞች ነገሮች ከሆኑት አንዱ ረኃብ ነው ።

ነቢዩ ኤርምያስ የረኃብን አደገኛነትና አሰቃቂነት አውስቶ ሲናገር "በረኃብ ከሞቱ ሰዎች ይልቅ በሰይፍ የሞቱ ይሻላሉ ብሏል ሰቆ. ኤር. ፬፡፱ ። እንደ ነቢዩ ኤርምያስ አባባል ሰዎችራኃብ ከጸናባቸው ለመብል ሲሉ እግዚአብሔርን እስከ መካድ ሃይማኖታቸውንም እስከ መለወጥ ይደርሳሉና ራብ ከማንኛውም መከራ የከፋ መሆኑን ያስገነዝባል ።

መቸም ራብም ሆነ ጥጋብ ከመጠኑ ካለፈ እኔነትን እንደሚያስረሳ የታወቀ ነው ከዚህ ላይ በባለ ጠግነትና በድኅነት ስለሚመጡ ችግሮች ጠቢቡ ሰሎሞን የተናገረውንና ወደ እግዚአብሔር ያመለከተውን እንመልከት "ድኅነትንና ባለጠግነትን አትስጠኝ ነገር ግን የሚያስፈልገኝን እንጀራ ስጠኝ ካለ በኋላ ምክንያቱን ሲገልጽ የጠገብኩ እንደሆነ ማነው እግዚአብሔር እንዳልልና እንዳልክደው የራበኝ እንደሆነ ደግሞ የሰውን ገንዘብ እንዳልሰርቅና በአምላኬም ስም በሐሰት እንዳልምል ነው" ብሏል ምሳ. ፴. ፰ ።

እንግዲህ ራብተኞች የሚባሉት በየአውራ ጎዳናዎች ተቀምጠው ኃላፊ አግዳሚውን እየጠበቁና የሰውን እጅ ተስፋ አድርገው የሚኖሩ እጅና እግራቸው የተቆረጠ ዓይናቸውም የፈረጠ ብቻ መሆናቸውን የሚያስቡና የሚገምቱ ሰዎች ይኖሩ ይሆናል ግን ራብ የሚያጠቃቸው አካለ ስንኩሎቹን ብቻ ሳይሆን ሙሉ ጤንነት ያላቸውም ከዚህ አያመልጡም ለምሳሌ በዘፍጥረት ፵፩.፶፬-፶፯ ድረስ የሰፈረውን ጽሑፍ እንደምንመለከተው በየሀገሩ ሁሉ ራኀብ ሆነ የግብጽም ምድር ሁሉ ተራበ ተብሎ ተገልጿል ይህ ሁሉ በሰውም በእንስሳም በጠቅላላ በደመ ነፍስ ሕያው ሁኖ በሚኖር ፍጡር ሁሉ እንጂ በተለዩና በአካለ ስንኩሎች ብቻ አልነበረም ።

ታድያ የዚሁ ዓይነት ችግር በሚደርስበት ጊዜ ገንዘብ ያለው ሁሉ ዝም ብሎ ማየት አያስፈልገም ችግር ለሚደርስባቸው ሊያዝንላቸው ሊራራላቸውና ሊረዳቸው ይገባል እንዲህ ማለት ከሚበለው ኅብስት ቆርሶ ቢያጉርሳቸው ከሚለብሰውም ልብስ ቀድዶ ቢያለብሳቸው ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር እንደ መስጠት ስለሚቆጠርና እግዚአብሔርም የዚህን ዓይነት ስጦታና ርኅራኄ ለሚፈጽሙ ሰዎች በልብ ያልታሰበውን በዓይን ያልታየውን ሀብት እንደሚሰጣቸው አያጠራጥርም "ስጡ ይሰጣችኋል" ተብሏልና ጦቢትም ኅብስት ለርኁባን የሚለው ቃል በእግዚአብሔር ዘንድ ምን ያህል ባለሟልነትን እንደሚቀዳጅ በመገንዘብ "እህሌን ለተራቡ ሰዎች ልብሴንም ለተራቆቱ ሰጠሁ" ብሏል መጽ.ጦቢ ፩፡፲፩። ኅብስት ለርኁባን የሚለውም ዘይቤ ትክክለኛ ትርጉም አገኘ የሚያሰኘው እንደዚህ ዓይነት ያለ ስጦታ ነው አዎ የራብ አደጋ ደርሶባቸው ለጽኑ ረኃብ ተጋልጠው የሚኖሩትን ሰዎች መርዳት በምድራዊ ዓለምም ሆነ በሰማያዊ ዓለም ታላቅ ስምና ክብር ነው ።

የተራቡትን መርዳትና ጦም አዳሪዎችን በቅርብ ሁኖ መቆጣጠር በሰው ላይ የደረሰውንም ችግር ማቃለልና በተቻለ መጠን መርዳትም በእግዚአብሔር ፊት ከፍተኛ አስተዋጽኦ መሆኑን ሲያስረዳ መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦቢትንና ጦብያን ጠርቶ የሰውን ጸሎትና ምጽዋት ወደ እግዚአብሔር ከሚያሳርጉ ከ፯ ሊቃነ መላእክት አንዱ እሱ ራሱ መሆኑን ከገለጸላቸው በኋላ የሚከተለውን መንፈሳዊ ምክር ሰጥቷቸዋል "ጸሎት ከምጽዋትና ከፍቅር ከሃይማኖትም ጋር ያማረና የተወደደ ነው ምጽዋት ታድናለች ከኃጢአትም ሁሉ ታነጻለችና ወርቅን ከማድለብ ምጽዋት መስጠት ይሻላል ምጽዋትንና ጽድቅን የሚያደርጉ ሰዎች ሁሉ ለራሳቸው ሕይወትን ያገኛሉ" ሲል በሰፊው አብራርቶ ነግሯቸዋል ጦቢት ፲፪፡፰-፱ ።

የተራበውን መርዳት ሰማያዊ ፀጋን የሚያድል መሆኑን የተገነዘበ ጠቢቡ ሰሎሞንም ድሀውን የሚያስጨንቅ ሰው ፈጣሪውን ይሰድባል ለድኃ ምሕረትን የሚያደርግ ግን ያከብረዋል ብሏል ምሳሌ. ፲፬፡፴፩ ።

ይሁን እንጂ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ "ሊሠራ የማይወድ አይብላ" የሚለውን ቃል ዘንግተውና የሥራን ክቡርነት ጠልተው ባለመሥራታቸው ራኃብን በፈቃዳቸው ወደቤታቸው የሚያስገቡ አይታጡም ምክንያቱም የሚያዩበት ዓይን የሚሄዱበት እግር የቆመውን የሚጥሉበት የወደቀውን የሚያነሱበት እጅ ሲኖራቸው ሠርተው በመጠቀም ፈንታ በማይረባና ጥቅም በማይገኝበት ቦታ መዞርና ሥራን ፈትቶ መዋል ራኃብን ወደቤት ጠርቶ እንደመጋበዝ የሚቆጠር ነው ስለዚህ በሥራ ተሰማርቶ ራስን መርዳት ቢቻልም ለተራቡ መትረፍ አስፈላጊ ነው ።

የሰው ልጅ በዓለም ውስጥ ሲኖር እንዲሁ በተአምራት ያለ እንጀራ ሕይወቱን አግኝቶ ጤናው ተጠብቆ ቁሞ ለመሄድ እንደማይቻለው በተለያዩ መጻሕፍት ተገልጿል ለምሳሌ ጠቢቡ ሲራክ የኑሮህ መጀመሪያ የምትበላው እህል የምትጠጣው ውሃና የምትለብሰው ልብስ ነው ብሏል ሲራ. ፳፱፡፳፩።

ስለዚህ ኅብስትን ለማግኘትና የተራበውን ሆድ ለመሙላት ባጭር ታጥቆ ላብን እያንጠፈጠፉ መሥራት ያስፈልጋል ራስን ለመቻል የተራበውንም ለመርዳት የሚቻለውም በሥራ መሆኑን መገንዘብ ያሻል ።

ጦቢት ከዚህ ከምድራዊው ዓለም



www.ethiopianorthodox.org

ለመጨረሻ በሞት ተሰናብቶ በሚሄድበት ወቅት ልጁ ጦብያን ጠርቶ ምጽዋትን ከመመጽወት ወደኋላ እንዳይልና ምጽዋትን በቸልተኛነት እንዳይመለከተው ሲመክረውና በጥብቅ ሲያስገነዝበው "ከእህልህ ለተራቡ ፣ ከልብስህም ለተራቆተ ሰው ስጥ የተረፈውንም ሁሉ ለምጽዋት አድርግ እህልህንም በጻድቃን መቃብር ላይ አሳድር (በድሆች ሆድ አሳድር) ሲል አስጠንቅቆታል ጦቢ. ፬. ፲፯ ።

አሁንም ቢሆን ራስን በራስ ለመርዳትና ረኃብን ከገጸምድር ለማውደምከመሬት ጋር መታገል ነው እንጀራ ከምድር ውስጥ ይወጣል" ተብሎ ተጽፏልና ኢዮ. ፳፰.፭ ። ቀደም ሲል ሕዝበ እግዚአብሔር ተብለው ይጠሩ የነበሩት የእስራኤል ሕዝብ ከግብጻውያን አገዛዝና ከፈርዖን ባርነት ነጻ ሁነው በሲና ምድረ በዳ ሳሉ ረኃብ ጸንቶባቸው ከመሰቃየታቸው የተነሣ (ብፁዕ ውእቱ ዘይበልዕ እምፍርፋራተ ማእዱ ለፈርዖን) ከፈርዖን ፍርፋሪ የሚበላ ንዑድ ክቡር ነው እስከ ማለት ደርሰው እንደ ነበርና "እኛን በረሀብ ልትገድሉን ወደዚች ምድረ በዳ አውጥታችሁናል በሥጋው ምንቸት አጠገብ ተቀምጠን እንጀራ ስንበላና ስንጠግብ ሳለን በግብፅ ምድር በእግዚአብሔር እጅ ምነው በሞትን" ዘጸአ. ፲፮.፫ በማለት በሙሴ ላይ አጉረምርመው ነበር ነገር ግን በመከራ ያሉትን የሚያድን ለተራቡት የሚያስብላቸው ለተበደሉ የሚበቀልላቸው እግዚአብሔር የደረሰባቸውን ጽኑ ረሀብ ተመልክቶ መናውን ከደመና እያወረደ በመመገብ ረሀባቸውን እንዳስወገደላቸው በዘጸአት ፲፮፡፲፬-፲፭ ላይ የሰፈረውን ጽሑፍ እናስታውሳለን ።

በዚህም አንጻር መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዚህ ዓለም ፴፫ ዓመት ከ፫ወር ሲኖር የታመመውን እያዳነ የሞቱትን እያስነሳ እንዲሁም ለተራቡት እንጀራን አበርክቶ ከመመገቡም በላይ ረኃበ ነፍስ ለጸናባቸው ራሱ የሕይወት እንጀራ ሆኖ እንደ ቀረበ ተጽፎአል ቃሉም እነሆ ከሰማይ የወረደው ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘለዓለም ይኖራል እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው ፤ በመሠረቱ የዓለም መድኅን ክርስቶስ የሕይወት ኅብስት ሁኖ ለምእመናን የቀረበው ምእመናኑ እንዲመገቡትና በዚሁም አማካይነት ከኃጢአታው ነጽተው ከእርሱ ጋር ተዋህደው እንዲኖሩ ነው ።

ስለዚህ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘትና ረሀበ ነፍስን ለማስወገድ መለኮት የተዋሃደውን ኅብስት ይመገብ የሰው ሕይወቱ ይህ ነውና ።

ከነፈርግብ ማርቆስ

# ደብዳቤዎች

ከገጽ ፳፬ የዞረ

፱ኛ/ አቶ ጽጌ ዓለሜ ከ14 ቀ. 17

ለቅዱስ ኢያቄምም በስሙ ታቦት ተቀርጾለታል ቤተ ክርስቲያንም ታንጾለታል በቅዱስ እያቄም ስም የታነጸው ቤተ ክርስቲያንም የሚገኘው በጐንደር ክፍለ ሀገር በጋይንት አውራጃ በስማዳ ወረዳ ልዩ ስሙም በራሱ በቅዱሱ ስም "እያቄም" እየተባለ የሚጠራ ነው ። በሌሎች ክፍላተ ሀገርም ሊኖር ይችላል በዓለ ዕረፍቱም የሚከበረው ሚያዝያ ፯ ቀን ነው በዚህም መሠረት በየወሩ በ፯ኛው ቀን ይታሰባል ማለት ነው ።



# ክቡር ሞቱ ለጻድቅ

ለሞት ስሙ እንደሚያመለክተው ሁለት ዓይነት መልክ አለው ። ይኸውም አንደኛው ሞት ነፍስ ከሥጋ መለየት ሲሆን ሁለተኛ ሞት ደግሞ ነፍስ ከሥጋ ከተለየች በኋላ መካነ ኵነኔ መሄድ ነው ።

ነፍስ ማደሪያዋ ከሆነው ከሥጋ ከተለየች በኋላ በእግዚአብሔር ያመነችና እግዚአብሔርን በሃይማኖትና በክርስቲያናዊ ተግባር ያገለገለች ከሆነች ከምድራዊ ዓለም ወደ ሰማያዊ ዓለም ከሥጋዊ ድካም ወደ ዘለዓለማዊ ዕረፍት ከሥጋዊ ሐዘንና ብስጭት ይህ ሁሉ ወደ ማይገኝበት መንፈሳዊ ደስታ በጠቅላላ ከጊዜያዊ ኑሮ ፍጻሜ ወደ ሌለውና በሕይወት ወደ ተከበበው ዓለም በክብር ትጓዛለች ።

በሠራችው ኃጢአት ከእግዚአብሔር የተለየችና በእግዚአብሔር ያላመነች ነፍስ ግን ከዚህ ዓለም በሞት ተለይታ በምትሄድበትና ከሥጋ በምትለይበት ወቅት ኃዘን እንጂ ደስታ ፣ ጨለማ እንጂ ብርሃን ወደ ማይታይበት ፣ ድካም እንጂ ዕረፍት ወደማይገኝበትና የሰላም ድምፅ ወደማይሰማበት ቦታ ትሄዳለች ይኸውም በዮሐንስ ራእይ በ፳፱ ፣ ፲፬ የተገለጸው ዳግም ሞት የሚባለው ነው ።

እንግዲህ የሃይማኖት መጽሐፋችን ባዘዘው ሕግና በክርስቲያናዊ ስነ ሥርዓት ያደጉ በመንፈሳዊ ተግባርና በሃይማኖት ጸንተው የኖሩ ሰዎች ከዚህ ዓለም በሞተ ሥጋ ሲለዩ ያለ አንዳችችግር በታላቅ ክብርና ደስታ ነፍሳቸው ትለያለች ነቢዩ ዳዊትም ቅዱሳን ከዚህ ዓለም ሲለዩ ምን ያህል ክብር እንዳላቸው አውስቶ ሲናገር "የቅዱሳን ሞት በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው ብሏል መዝ ፻፲፭፣ ፲፭ ዳዊት እንዲህ ማለቱ የጻድቃን ነፍስ ተዋህዳው ከነበረችው ከሥጋ ስትለይ በመዓዛ ገነት ተመስጣ በቅዱሳን መላእክት ጣዕመ ዝማሬ ታጅባ መላእክትና ሊቃነ መላእክትም ከበዋት ወደ እግዚአብሔር ስለምትደርስ ፍርሃትና ድንጋጤ የሌለባት መሆኑን ለመግለጽ ነው ።

እውነትም ዳዊት እንደተነበየው ጻድቅ ሲሞት ጻእረ ሞት አይደርስበትም ፍርሃትም አይሰማውም በዚህም መሠረት የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል ከሚባሉ ጻድቃን መካከል አንዱ አቡነ ተክለ ሃይማኖት መሆናቸውን እናስታውሳለን አቡነ ተክለ ሃይማኖት በነበሩበት ዘመን ጥቂት ጊዜ ስንኳ ያለ ሥራ ያሳለፉበት ጊዜ እንዳልነበረ የሕይወት ታሪካቸው ይገልጽልናል በተለይ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸሁ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እያስተማራችኋቸው የእናንተ ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው ሲል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በማቴዎስ ወንጌል ፳፰ ፣ ፲፱-፳ የተናገረውን ቃልና ያዘዘውን አምላካዊ ትእዛዝ ለመፈጸም በኢትዮጵያ እየተዘዋወሩ ስብከተ ወንጌልን በማስፋፋትና የወንጌል ትምህርት ላልደረሳቸው በማዳረስ መንፈሳዊ ተልእኮአቸውን የፈጸሙ ታላቅ ሐዋርያ ናቸው ።

አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን ሲያስተምሩ ይደርስባቸው የነበረው ሥቃይና መከራ ይህ ነው ተብሎ አይነገርም ነበር በተለይ በሲዳሞ ሀገረ ስብከት በወላይታና በአካባቢው ጣዖትን በሚያመልኩ በእነ መተሎሚ ይደርስባቸው የነበረው እሥራትና ግርፋት ገድላቸው እንደሚያስረዳው ሐዋርያት ይቀበሉት ከነበረው ጽዋትወ መከራ ቢበዛ እንጂ የሚያንስ አይመስልም ።

ነገር ግን አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን በሚያስተምሩበት ወቅት ቢገረፉና ቢታሠሩም ግርፋቱንም ሆነ እሥራቱን ኢምንት ሳይቆጥሩ "ሩጫዬንና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበልኩትን አገልግሎት እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈጽም ዘንድ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደ ማከበር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ" የሐ. ሥራ ፳ ፣ ፳፬ በማለት የወንጌልን ትምህርት ዕለታዊ ተግባራቸው አድርገው መላ ዘመናቸውን ሲደክሙ ኑረዋል ።

እንዲያውም አቡነ ተክለ ሃይማኖት ወንጌልን በማስተማር በፈጸሙት ሐዋርያዊ ተልእኮ መንፈሳዊ ተልእኮዋቸውን የሚያበሥር "ሐዲስ ሐዋርያ መትልወ ቶማስ ሰማዕት በስባረ እግሩ ዘቆመ መጠነ ሰብአቱ ዓመት" ሲል አንድ ደራሲ መስክሮላቸዋል ።

ጠቢቡ ሰሎሞንም የእግዚአብሔርን ቃል በማስተማር ስለሚደክሙ ቅዱሳን ሲገልጽ የጻድቅ ከንፈሮች ብዙ ሰዎችን ይመግባሉ ሰነፎች ግን ከልባቸው ጉድለት የተነሣ ይሞታሉ ብሏል ምሳ. ፲ ፣ ፳፩ ይህንንም ተከትለው አቡነ ተክለሃይማኖት የእግዚአቤሔርን ቃል ለተራቡት ትምህርትን በመመገብ ክርስቲያናዊ መንገድ ጠፍቷቸው በጨለማ ሲጓዙ ለነበሩትም የወንጌልን ብርሃን በማብራት ሕይወት ወደ ሚመነጭበት ሕገ ወንጌል እየመሩ ብዙዎቹን ሰዎች መልሰዋል በዚህ መልክ ለብዙ ዘመናት ሲሠሩና "ሂዱና አሕዛብን ሁሉ አስተምሩ" የሚለውን የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስንም መመሪያ በመጠበቅ መንፈሳዊ ተልእኮዋቸውን ፈጽመው በ፺፱ ዕድሜያቸው ከዚህ ብርሃንና ጨለማ ሐዘንና ደስታ እየተፈራረቁበት ከሚኖረው ዓለም ነሐሴ ፳፬ ቀን ፲፪፻፺፯ ዓ.ም. አርፈዋል አዎ እነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የተሰጣቸውን አደራ ተቀብለው ከኖሩ በኋላ ወደ ማያልፈው ዓለም እንደ ሄዱና ግዳጃቸውን ፈጽመው እንዳረፉ ተጽፏል ።

ዛሬ በእነ አቡነ ተክለ ሃይማኖት እግር ተተክቶ ቅዱስ ወንጌልን አንግቦ ለማስተማር የሚፋጠነውና የወንጌልን ቃል በትክክል ለመመስከር የሚነሳ ማን ይሆን ? ባሁኑ ጊዜ የወንጌል ትምህርት ጠምቷቸው ኧረ የመምህር ያለህ እያሉ በየሀገረ ስብከቱ ጩኸታቸውን የሚያስተጋቡ በጥቂቱ የሚገመቱ አይደሉም ነገር ግን ጩኸታቸውን ሰምቶ የሚያቀርቡትንም ጥያቄ ተቀብሎ የሚረዳቸውና ከደረሰባቸው የትምህርተ ወንጌል ጥም ሊያረካቸው የሚችል አስተማሪ ያስፈልጋቸዋል ።

ከነፈርግብ ማርቆስ



www.ethiopianorthodox.org

# ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተ ሰብእ ፡

(በከፍ ያለው መሪጌ)

## ቤተ ክርስቲያን የማን ናት ?

ቤተ ክርስቲያን የወል ናት ፡ ክርስቶስ ክርስቲያን (መሃሚውያን) የሆኑ ሁሉ በአንድነት ተሰብስበው አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚፈጽሙባት የጸሎት ቤት ናት ። የወል ናት ሲባል ፤ ጻታን ፤ ዕድሜን ፤ ዘርን ፤ መደብን አትለይም ፤ ሀልወተ እግዚአብሔርን ወይም የእግዚአብሔርን መኖር የሚያምን ሁሉ በተለይም ክርስትናን የተቀበሉ ወገኖች የእግዚአብሔርን ሕገ መንግሥት ማለት አሠርቱ ትእዛዛተ አሪትንና ስድስቱን ቃላተ ወንጌል ለሰው ሁሉ የሕይወቱ መመሪያ እንዲሆኑ የተሰጡትን ሕግጋት የሚማሩባት መንፈሳዊት ትምህርት ቤት ናት ። በሌላ አነጋገር ምዕመናን በአንድ ላይ በኅብረት ሁነው ጡዳሴን ቅዳሴንና ዝማሬን ለፈጣሪያቸው የሚያቀርቡባት የመዝሙር አዳራሽ ናት ። በዚህ ረገድ ቤተ ክርስቲያን የኅብረተሰብእ አገልጋይ ስትሆን ፤ ኅብረተ ሰብእም የቤተ ክርስቲያን ደጋፊ መሆኑ አይዘነጋም ። በመሠረቱ ኅብረተ ሰብእ በትምህርትና በልማት ጉዳና ለሚያደርገው ፈጣን ግሥጋሴ ቤተ ክርስቲያን እንደ ነፍስ መንግሥት እንደአካል ሁነው በኅብረት ይሠራሉ ። ምንጊዜም ቢሆን ለሞራልና ለሃይማኖት ጥያቄዎች ቤተ ክርስቲያን መልስ ትሰጣለች ለምሳሌ አንድ ሱንዳር ሲንግ የተባለ ሕንዳዊ ሰማዕት እንዲህ ሲል ተናግሮአል ሕያው እግዚአብሔር ባልተወሰነ ቸርነቱ የሕንድን ሕዝብ ከቅኝ ገዥዎች ባርነት ነፃ ለማውጣት ማኅተመ ጋንዲን አስነሣላቸው ፤ እንደዚሁም መንፈሳዊ ረሀብ እንዳያጠቃቸው ሐዋርያና ሰማዕት የሆነውን ቅዱስ ሱንዳር ሲንግን አስነሣላቸው ይላል ።

ዛሬም ቢሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ስናየው ቤተ ክርስቲያን ስለ ሰላም ፤ የሃይማኖት ነፃነት ፤ ስለሰው ዘር እኩልነት በጥብቅ ትከራከራለች ። ምክንያቱም የቤተ ክርስቲያን መሥራች የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አይሁዳዊም ሆነ አረማዊ ሁሉን ነገድ በእኩልነት ዓይን ይመለከታቸው እንደነበርና በጉባኤውም ሆነ በማዕዱ በአንድነት ይሰለፉ እንደነበር ቅዱሳት መጻሕፍት ያስረዳሉ ። ስለዚህ በእግዚአብሔር መንግሥት የሰዎች ሁሉ እኩልነት ተረጋግጧል ። "ተመልከት ዓላማህን ተከተል አለቃህን" እንዲሉ ዛሬም ቤተ ክርስቲያን የሊቀ ካህናት ክርስቶስን ፈለግ በመከተል የሰዎችን እኩልነትና መብት ለማስከበር የደወል ድምፅዋን ከማሰማት ወደኋላ አላለችም ። ለምሳሌ በደቡባዊ አፍሪካ ያለች ቤተ ክርስቲያን ክፉ መንፈስን ፤ ዘረኝነትን ፤ ምዝበራንና ጭቆናን በመቃወም ስለኅብረተሰብእ መሠረታዊ መብቶች የቆሙት የሃይማኖት መሪዎችዋ ከፍተኛ ተጋድሎ በማድረግ የሐዋርያነትና የሰማዕትነት ሥራ እየሠሩ ናቸው ። በዚሁ በደቡብ አፍሪካ የሃይማኖት ነፃነት አለ ቢባልም ነገሩ ዕንቆቅልሽ ነው ። አንድ ነፃ ኅብረተ ሰብእ በነፍሱም ሆነ በሥጋው ሕያው እንዲሆን ያስፈልጋል ፤ ሐቁም ይህ ነው

ስለዚህ ነው ለኅብረተሰብእ ደኅንነት ሲባል ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ድርና ማግ ወይም ሰምና ወርቅ ሁነው ለሀገር ብልጽግና ለኅብረተ ሰብእ አንድነትና ደኅንነት የሚሠሩት ። በመሠረቱ የሃይማኖት ነፃነት ከሶሻል ፤ ከኢኮኖሚና ከፖለቲካ ነፃነት ተለይቶ ብቻውን አይታይም ። ለምሳሌ የክርስትና ሃይማኖት መሥራች የሆነው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይመራውና ያስተምረው የነበረውን ኅብረተሰብእ ስለእግዚአብሔር መንግሥት ብቻ አልነበረም ያስተማረው ። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን መንግሥት ጽድቁንም ፈልጉ ይልና የዕለት ሲሳያቸውም እንዳይጓደል ዳቦ ቆርሶ ዓሣ አበርክቶ እንደመገባቸው በወንጌል ተጽፎአል ።

ስለዚህ ነው የኅብረተሰብእን ደኅንነት ለመጠበቅ መንግሥት እንደ አካል ቤተ ክርስቲያን እንደ ነፍስ ሆነው የሚሠሩት በልምድ እንደሚታወቀው ሁሉ ለሥጋዊ ሕይወት መጠገኛ ሥጋዊ ምግብ ያስፈልጋል ፤ እንደዚሁም ለመንፈሳዊ ሕይወት መንፈሳዊ ትምህርት ወይም ቃለ እግዚአብሔርን መመገብ አስፈላጊ ነው ። መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል ሰው በእንጀራ ብቻ አይኖርም ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው ቃልም እንጂ ማቴ. ፬፡፬ ።

ስለዚህ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ለሀገር ዕድገት ለኅብረተ ሰብእ ደኅንነት (ነፍስና አካል ሁነው) ይሠራሉ ። ያለነፃነት ሀገር ትርጉም የለውም ፤ ሃይማኖትና ነፃነትም ተነጣጥለው አይታዩም ። ምክንያቱም ነፃነት ከሌለ ሰዎች አምልኮተ እግዚአብሔርን በሰላም ሊፈጽሙ አይችሉምና ነው ። ሳይንስና ሃይማኖት ሁሉም ለሥልጣኔ ዕንቅፋት አይሆኑም ፤ ከሰው ዘር የሥልጣኔ ታሪክ እንደምንረዳው አንድ ኅብረተሰብእ በአእምሮ እየበለጸገና እየመጠቀ ሲሄድ ስለ አካባቢውና ስለሚኖርባት ዓለም እራሱን ይጠይቃል ። ይህም በጥንት ግሪካውያን ፤ ባቢሎናውያንና ሮማውያን የተረጋገጠ ነው ። ከታሪክ መዝገብ እንደምንረዳው እንዲህ ሲሉ ጠይቀዋል ። ዓለማት ከየት ተገኙ ? በማን ወይም በምን ተፈጠሩ ? የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ዓለማት ሁሉ የተፈጠሩት በእግዚአብሔር ሥልጣን ነው የሚል ሲሆን የሳይንስ መልስ ግን ሌላ ነው ። በእርግጥ ሳይንስ ይመረምራል ፤ ሃይማኖት ይተረጉማል ፤ ሳይንስ ኃይል የሆነውን እውቀት ለሰው ይሰጣል ። ሃይማኖት እራስን የመቆጣጠር ጥበብ ወይም ማስተዋልን ለሰው ይሰጣል ፤ ብዙ ጊዜ ሳይንስ ከተጨባጭ ነገር ጋር ይሄዳል ፤ ሃይማኖት ቀጋን ከመስጠት ጋር ይዛመዳል ። በዚህ ረገድ ሳይንሳዊ ምርምርንና ሃይ

ተከታዩን በ፲፩ኛው ገጽ ይመልከቱ



# የድርሰት አጻጻፍ ዘዴና የንግግር ጥበብ

## ኃይለ ቃል

ቃል ከሰው ሐሳብ ጋር እንደነፍስና ሥጋ የመዋሐድ ጠባይ አለው ።

ቃላት የመሥራትም የማፍረስም ኃይል አላቸው እግዚአብሔር "ለይኩን ይሁን" ብሎ በተናገረው አንድ ቃል ብቻ ይህ ሁለንታዊ የሆነ ግዙፍ ዓለም ሊፈጠር ችሏል ።

ደግና ክፉውን ለይታ ከምታስታውቀው ዛፍ ፍሬ እንዳትበላ ሲል እግዚአብሔር ለመጀመሪያው ሰው የሰጠው አንድ የትእዛዝ ቃል በመሻሩ ብቻ የሰው ዘር ሁሉ ግንድ የነበረው አዳም ከነሚስቱ ከገነት እንዲባረር ተፈርዶበት ምድረ ፋይድ መውረዱ ተጽፎአል ነገሩ በዚህ ብቻ ሳያበቃ ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ ሞት ተከተለ ዘግየት ብሎም "ከልጅ ልጅህ ተወልጄ አድንሃለሁ" የሚል የተስፋ ቃል በመናገሩ ብቻ ወልደ እግዚአብሔር ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል እመቤታችን ተወልዶ ዓለምን አዳነ ።

ቃል ራሱም የክርስቶስ መጠሪያ ስሙ ነው ። ታዲያ ለይኩን ብሎ ይህን ዓለም የፈጠረ ያ ቃል እንደገና ዓለምን ለማሣለፍ የሚችል መሆኑ ታውቋል ሰውን በመልካችን እንፍጠረው ብሎ ሰውን የፈጠረ ያ ቃል ለጻድቃን የሚፈርድላቸው በኃጥአንም የሚፈርድባቸው በመሆኑ የአስፈሪነት ግርማ አለው ።

ዳዊትም በመዝሙሩ ቃለ እግዚአብሔር ይመትርነደ እሳት የእግዚአብሔር ቃል የሚንበለበለውን ነደ እሳት ይቆራርጣል በረሃውን ያናውጣል ፤ ዝግባውን ይሰባብራል ወዘተ የሚልም ተጽፎአል ባለቅኔውም ይህን መሠረት በማድረግ በረድ ቃልከ በጊዜ ዘንመ
የብሰ ዕፅ ድኅረ ኮነ ፆመ

ወዘየብሰ አሕየወ ዳግመ (በረዶ ቃልህ በዘነመ ጊዜ ለምልሞ የነበረው ዛፍ ሁሉ ደረቀ ፤ የደረቀው ዛፍ ለምልሞ አሸበረቀ ፤ እንደማለት ነው) ሲል ወስዶታል ።

ከዚህም ሁሉ ጋር "በዕውነት ቃሌ እንደ እሳት ድንጋዩንም እንደሚያደቅ መዶሻ ነው " የሚለውንም ቃል በኤር ፳፫ ፡ ፳፱ ይመልከቱ ።

ሐናንያ የተባለ የግል ጥቅም ፈላጊና ከማኅበራዊ ሥርዓቱ ኑሮ ለማፈንገጥ የተመኘ አንድ ግለሰብ ከራሱ መሬት ሽያጭ ሰርቆ በከፊል በማስቀረቱ" ርስትሕን የሸጥኸው ለዚህን ያህል ነውን? የሚል ጥያቄ ቀርቦለት "አዎ" የሚል የአንድ ቃል መልስ ብቻ እንደሰጠ ወዲያውኑ ሞት ተፈርዶበታል (የሐዋ.፭ ፩.፲፩)

በቃለ እግዚአብሔር ጸንዐ ሰማያት ሰማያት ከእግዚአብሔር ቃል የተነሣ ጸንተው ይኖራሉ የሚልም ክፍል አለ። ደግሞም እርሱ በተናገረ ጊዜ ዓለም ተፈጠረ ። (መዝ.፴፪፡፱)

በዓለማዊም ሥርዓት ቢሆን ለጥቅም ም ሆነ ለጉዳት በመዋል ታላላቅ ኃይላት የተገለጡባቸው ብዙ ቃላት አሉ። ለምሳሌ ኢትዮጵያ ከጣሊያን መንግሥት ጋር በሰላም አብሮ እየተረዳዱ የመኖርና የመደጋገፍ ውል በውጫሌ ሲዋዋሉ በትርጉም ተጣሞ የገባ አንድ ቃል ብቻ (፲፯ኛው አንቀጽ) ከባድ ችግር ፈጥሮ በመገኘቱ ብቻ ውሉ ፈርሶ የዓድዋን ጦርነት አስከትሏል ። ስለዚህም የቃል ትርጉም እንደቀላል ነገር የሚታይ አይደለም ። የዓለም መንግሥታት ሺህ ጊዜ ተፈራርመውበት ሺህ ጊዜ ሲፈርስ የሚኖረው ውል መቅኖ አጥቶ የሚቀረው በቃላት ትርጉም መዛባት ጭምር ነው ።

እንዲያውም ቃላት ዓለምን ያናውጣሉ የሚል አነጋገር አለ ። ስለዚህም በተለይ ግሥነት ያላቸው ቃላት የበዛበት ድርሰት ቅኔም ሆነ ንግግር የተለየ ኃይልና ውበት ይኖረዋል ። የግሥ መብዛትም ለዓረፍተ ነገሮች ግጠርና ለድርሰት ግልጥነት ተጨማሪ ውበት የሚሰጥ መሆኑ ታምኖበታል ። ስለግሥ ቃላትም አጠቃቀም ዘዴ በተከታዩ ቁጥር እንገልጣለን ፤ የዚህንም አገላለጥ መሠረተ ሐሳብ በይበልጥ መገንዘብ ለምትፈልጉ አንባቢዎች የምንጠቁማችሁ "ሥልጣኔ ማለት ምንድነች ?" የተሠኘችውን የአቶ ከበደ ሚካኤል መጽሐፍና "የፍልስፍና ትምህርት" በሚል ርእስ ዶ/ር የማነብርሃን ግርያም የጻፉትን ቅፅ ፪ መጽሐፍ እንድትመለከቱ ነው ።

ቄስ መክብብ አጥናው

## ዜና ሊቃውንት

ከገጽ ፲፱ የዞረ

ልክ ይቅርታ ተጠይቀው የነጋድራስነት ማዕረግና ከፍተኛ የሆነ የሥራ ኃላፊነት ቢሰጣቸው ሥራውን ተቀብለው ማዕረጉን አለመቀበላቸውን አስታውቀዋል ።

በወቅቱም ማለት በ፲፰፻፺፬ ዓ.ም የነበረው የፖለቲካ ይዘትና አንገብጋቢው ተግባር የውጫሌ ጉዳይ ስለነበረ በዚህ ረገድ ሊቁ የሥራ ተካፋይ እንዲሆኑ ተደርጉ ከፍተኛ የሆነ የሥራ ድርሻ አበርክተዋል ።

በተከታታይም የሐረር ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በመሆን እንዲሁም የምሥራቅ ጉምሩክ ጽሕፈት ቤትን በማቋቋም ሠርተዋል (ባሕሩ ታፍላ ከጻፈው የአለቃ አፅሜ ታሪክ)

ሊቁ ዓፅመ ጊዮርጊስ በትምህርትበሀገር ፍቅር በፖለቲካ ይዘት የበሰለ አስተያየት እንደነበራቸው የታሪክ ሰዎች ያረጋግጣሉ ።

ሆኖም ደንቆሮውን ሆነ ብልሁን ታታሪውንም ሆነ ሰነፉን በእኩልነት ደረጃ የሚመለከት የሞት ጥሪ ደርሶአቸው ከላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት በሞት ተለይተዋል ።

ከአሊቃ ዓምደ ጽዮን ተሰማ



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ሩፋኤል

ለመላእክት ብዙ ዓይነት የተልዕኮ
ሥራ አላቸው ከብዙዎቹ ሥራዎች
አንደኛው ፍጥረቱን ሁሉ እንደዘበኛ
ሆነው መጠበቅ ነው ፡፡

መላእክት የሰው ልጆች ደግ በሠሩ
ጊዜ ዕድሜ ሲለምኑና ሲያማልዱ ፣ ክፋት
በሠሩ ጊዜ ደግሞ ሞታቸውን ፣ ጥፋታ
ቸውን ሲለምኑ የሚኖሩና በሕይወታቸ
ው መጨረሻ ላይ ግን በሕይወት ሳሉ
የሠሩትን ሁሉ የሚመሰክሩ ናቸው ፣ ስ
ለዚህም ሰው የሠራውን (የተናገረውን
ም ክፉ ሥራ ሁሉ ወደ እግዚአብሔር
አድርሰው የሚያስፈርዱ መላእክት መ
ሆናቸው የተረጋገጠ ነው ፡፡

ቅዱሳን መላእክት በተልዕኳቸውና
በአገልግሎታቸው እጅግ በጣም የሚፋ
ጠኑና ረቂቃን በመሆናቸው ክቡር
ዳዊት ሲናገር "መላእክትን መንፈስ
የሚያደርግ አገልጋዮቹንም ነበልባል"
ብሏል መዝ ፻፫. ፬ መላእክት ለርዳታ
የተፈጠሩ በመሆናቸው በማንኛውም
ዕለት በማንኛውም ሰዓት በየትኛውም
ቦታ ለአማላጅነት ቢጠሯቸው ለእርዳታ
ቢማፀኑአቸው ፈጥነው ይደርሳሉ ፡፡

መላእክት የእግዚአብሔርን ሕግና
ትእዛዝ ጠብቆ ለሚማፀንባቸው ሁሉ ፣
ፈጥነው የሚደርሱና የሰውንም ወገን በ
ማንኛውም መንገድ የሚረዱ መሆናቸ
ው ቢታወቅም የእያንዳንዱን መልአክ
አገልግሎት በዚህ አጭር ጽሑፍ ለመግ
ለጽ አይቻልም በዚህ ጽሑፍ ለመግለጽ
የምፈልገው ግን ስለ ቅዱስ ሩፋኤል
ነው ፡፡ ቅዱስ ሩፋኤል ከሰባቱ ሊቃነ
መላእክት አንዱ ሲሆን እንደ ቤተ ክር
ስቲያናችን ሥነ ሥርዓት ጳጉሜን ሦስት
ቀን ይከበራል ፡፡

ነቢዩ ሄኖክ ስለመላእክት በተናገረ
በት አንቀጽ ላይ ሲገልጽ የአራቱን
መላእክት ቃል ሰማሁ ይልና የአንደኛ
ውን መልአክ ስምና ሥራ በዝርዝር
ከገለጸ በኋላ ሁለተኛውም መልአክ በበ
ሽታው ሁሉ ላይ በሰው ልጆችም ቁስል
ላይ የተሾመ ቅዱስ ሩፋኤል ነው አለ
ኝ" ብሏል መ/ ሄኖክ ፲. ፲፫ ፡፡

መላእክት የሰውን ልጅ የሚረዱት
የሀገሩን ሰው በመምሰል በቋንቋውና
በባሕሉ ሥነ ሥርዓት በመራመድ
ነው ቅዱስ ሩፋኤል በሰው አምሳል በመ
ገለጽ ከሠራቸው ተአምራት አንዱን
ክፍል ብቻ በዚህ ጽሑፍ ላይ እንአመለ
ከታለን ፡፡

አንድ ጦቢት የሚባል ሰው ነበር ፡፡
ይህ ሰው የተቸገረውን በገንዘብ የደከመ
ውን በጉልበት ከመርዳቱም ሌላ የሞተ
ውንም መቅበር ለእግዚአብሔር ሲል
ከሚፈጽማቸው መንፈሳውያን አገልግ
ሎቶች አንደኛው ክፍል ስለነበር ሰው
ሞተ የሚል ወሬ ከሰማ ፀንን ሳይቀብር
እህል ውሃ አይቀምስም ነበር ፡፡

በእምነትም በኩል ወገኖቹ ደማሊና
በዓል ለሚባሉት ጣዖታት ሲንበረከኩና
ሲሰግዱ ሲወድቁና ሲነሡ ጦቢት በእግ
ዚአብሔር ብቻ ያለውን እምነት እጅግ
በጣም አጠንክሮ ይኖር ነበር ፡፡

ወላጆቹ ገና በሕፃንነት ዕድሜ ሳለ
ጥለውት ስለሞቱ ጦቢት ለአካለ መጠን
ሲበቃ ሐና የምትባል ሚስት አገባ
ከዕለታት አንድ ቀን ከቤተ መቅደስ
ዕድሞ ተጠግቶ ተኝቶ ሳለ ወፎች ከዓይ
ኑ ላይ ኳሱበትና ብጉር ወጥቶ ዓይኑ ታ
ወረ ጦቢት ከአንዳንድ ሰዎች ልዩ ልዩ
ተግዳሮትን ስለሰማ በሐሰትና በውርደ
ት ተገዳሮትን ሰምቻለሁና ኃዘንም በዝ
ቶብኛልና ከመከራዬ እሰናበት ዘንድ
ለዘለዓለም ጸንቶ ወደሚኖር ወደ መቃ
ብር እሄድ ዘንድ እዘዝ ፣ ገጸ ረድኤትህን
ከእኔ አትመልስ በማለት ወደ እግዚአብ
ሔር ጸለየ ፡፡

በዚህም ጊዜ ጦቢት ከሚዶኑ ሰው
ከገባኤል በአደራ መልክ ያስቀመጠው
ገንዘብ ትዝ አለውና ልጁን ጦብያን
ጠርቶ የሚዶን ሰው ከሚሆን ከገባኤል
ዘንድ አደራ ያስቀመጥኩት ገንዘብ አለና
ሂደህ አምጣ አለው ጦብያም አባቴ
ሆይ ፣ ያዘዝከኝን ሁሉ እሠራለሁ ነገር
ግን ሀገሩን ስለማላውቀው ማን ያሳየ
ኛል አለው አባቱም ሀገሩንና ቦታውን
የሚያመለክት ደብዳቤ ሰጠውና ደመ
ወዝ (አበል) ሰጥቸው አብሮህ የሚሄድ
ሰው ፈልግ አለው ጦብያም አብሮት
የሚሄድ ሰው ሲፈልግ ቅዱስ ሩፋኤልን
በሰው አምሳል አገኘና የሚሄድበትን
ሀገርና የአባቱን ገንዘብ በአደራ መልክ
ተቀብሎ ያስቀመጠውን ሰው ቢጠይቀው
መንገዱንም ሀገሩንም አውቀዋለሁ
በገባኤልም ቤት ስለነበርኩኝ ሰውየ
ውን በሚገባ አውቀዋለሁ አለው ፡፡

ጦብያ በቅዱስ ሩፋኤል አነጋገር
በጣም ተደስተና ለአባቴ እስከምነግ
ረው ድረስ ከዚሁ ቆየኝ እንዳንጠፋፋ
ወዲያና ወዲህ አትበል ብሎ ወደ አባቱ
ሄደና ነገረው አባቱም ጥራውና ልጠይ
ቀው አለው ጠርቶ ሲያመጣው ጦቢት
ሩፋኤልን የት እንደሆነ ቢጠይቀው
እኔ የታላቅ ወንድምህ የአናንያ ዘመድ
አዛርያ ነኝ ስላለው በጣም ተደስተና
በቀን በቀን አንዳንድ ወቄት እንሰጥሃለ
ን ምግብ ከልጄ ጋር የልጄን ስንቅ አብ
ራችሁ ትመገባላችሁ ስትመለስ ከዚህ
የበለጠ ገንዘብ እሰጥሃለሁ በማለት ነገ
ሩን ከጨረሰ በኋላ ጦብያና ሩፋኤል
መንገዳቸውን ቀጠሉ ፡፡

ሲጓዙ ውለው ማታ ከፈሳሽ ውሀ
አጠገብ ደረሱና በዚያው አደሩ ጦብያ
ወደውሃው ወርዶ ሲታጠብ ታላቅ ዓሣ
ከውሃው ወጥቶ ጦብያን ሊውጠው ቀረበ
በዚህ ጊዜ ቅዱስ ሩፋኤል አይዞህ አት
ፍራ ዓሣውን ያዝና ወደ ውጭ አውጥተህ
እረደው ጉበቱንና ልቡን ሐሞቱንም
አውትጠህ ያዝ አለው ጦብያም እንዳ
ዘዘው አደረገ ዓሣውንም ጠብሰው ከበሉ
በኋላ ጦብያ ወንድሜ አዛርያ ሆይ የዚህ
ዓሣ ሐሞቱና ጉበቱ ለምን ይጠቅማል ?
አለው መልአኩም ክፉ ጋኔን ያደረበት
ሰው ቢኖር ጉበቱና ልቡ ለዚያ ሰው
በፊቱ ያጤሱበታል ሴትም ብትሆን
ያጤሱላታል ከዚያ በኋላ አይታመምም
አትታመም ሐሞቱንም ደቁሶ የበሽተኛ
ውን ዓይን የኳሉት እንደሆነ ይድናል
አለው ጦብያና አዛርያም ራጊስም ወደ
ምትባል መንደር በተቃረቡ ጊዜ ቅዱስ
ሩፋኤል ጦብያን ራጉኤል ከሚባለው
የዘመድ ቤት እንደሚያድሩና ለእርሱም
ልጁን እንደሚድርለት አበሠረው ጦብ
ያ ግን የልጅቷን ታሪክ ቀደም አድርጐ
ሰምቶ ስለነበር ወንድሜ አዛርያ ያችን
ልጅ ሰባት ወንዶች አግብተዋት ሁሉም
ወዲያውኑ እንደሞቱ ሰምቻለሁ እኔም
አሁን እርሷን ባገባ ወዲያውኑ እሞታ
ለሁ አለው ፡፡

ቅዱስ ሩፋኤል ወደጫጉላው ቤት
በገባህ ጊዜ የደቀቀ ዕጣን ከዓሣው ጉበት
ጋር አጢስ ያ በሸተተው ጊዜ ጋኔኑ ይሸሻል
ለዘለዓለምም አይመለስም ስላለው በጣ
ም ደስ አለው መልአኩ ሩፋኤልና ጦብያ
ይህንን ከተነጋገሩ በኋላ ወደራጉኤል
ቤት ሄዱ ራጉኤል ምግብ አቅርቦላቸው
ከተመገቡ በኋላ ከዘመዱ ከጦቢት ተል
ከው መምጣታቸውን ስለነገሩት እጽፍ
ድርብ ደስታ ተሰማው ወዲያው ቅዱስ
ሩፋኤል ልጁን ሣራን ለጦብያ እንዲሰ
ጠው ራጉኤልን ጠየቀውና በደስታ
ስለሰጠው ጦብያ ሣራን ይዞ ወደጫጉ
ላው ሲገባ መልአኩ እንደነገረው የደቀቀ
ዕጣን አምጥቶ የዓሣውን ጉበቱንናልቡን
ጨምሮ አጤሰው ጢሱ በሸቱተው ጊዜ
ያ ጋኔን ሸሽቼ አመልጣለሁ ሲል ቅዱስ
ሩፋኤል አስሮ አግዞታል ፡፡

በዚያች ሌሊት ሁለቱ ጦብያና ሣራ
አብረው አደሩ ምንም ጉዳት አልደረሰ
ባቸውም ራጉኤልም እግዚአብሔርን
አመስግኖ ልጁን ሣራን ወደ አባቱ ቤት
ይዟት እንዲሄድ ለጦብያ ፈቀደለት ከዚ
ያ በኋላ ወደ ገባኤል ሂደው ከገባኤል የ
ተቀመጠውን ንብረት ከተቀበሉ በኋላ
ወደ ቤታቸው ጉዟቸውን ቀጠሉ ወደ
አባቱ ጦቢት በተቃረቡ ጊዜቅዱስ ሩፋ
ኤል ለጦብያ ያንን ሐሞት ወስደህ አባ
ትህን ኳለው ከዕውርነቱ ይፈወሳል አለ
ውና እንደነገረው ቢያደርግ የአባቱ
ዓይን በርቷል ፡፡ ጦቢያ አዛርያን ጠርቶ
ከአንተ ጋር ያመጣሁትን ገንዘብ እኩሌ
ታ ይዘህ በተድላ በደስታ ሂድ አለው ፡፡
እስከ አሁን ድረስ መልአኩ ሩፋኤል
መሆኑን አልተረዱም ነበር መልአኩ ሩ
ፋኤል ሁለቱን ጦብያንና ጦቢትን ጠር
ቶ እግዚአብሔርን አመስግኑት ለእር
ሱም ተገዙ ለስሙም ምስጋና አቅርቡ
ስላደረገላችሁ በጎ ነገር ሁሉ በሰው ሁ
ሉ ፊት እመኑበት የእግዚአብሔርን ክብ
ር ተአምራቱንም ግለጡ ለእርሱ መገዛ
ትን ቸል አትበሉ ፡፡

ካለ በኋላ እንዴት እንደረዳቸው ሲገ
ልጽ "ምራትህ ሣራና አንተ በጸለያችሁ
ጊዜ ልመናችሁን ወደ እግዚአብሔር አ
ደረስሁ አንተም በጎ ሥራን መሥራት
ባልዘነጋህ ጊዜ እኔ ከአንተ ጋር ነበርኩ
የሁሉ ገዥ የሆነ እግዚአብሔር አንተን
አድንህና ረዳህ ዘንድ ወደ አንተ ላከኝ
የቅዱሳንን ጸሎት ከሚያሳርጉ ወደ
ከበረ ወደ እግዚአብሔር ጌትነትም
ከሚያገቡ ከከበሩ ከሰባቱ አንዱ አለቃ
እኔ ሩፋኤል ነኝ አለው መ/ጦቢት
፲፪ ፡ ፲፭

ጦቢያና ጦቢት እስከዚህ ድረስ
ቅዱስ ሩፋኤል መሆኑን አላወቁም
ነበር የሚረዳቸው በሰው አምሳል ነበ
ርና ከላይ የተነገረውን ቃል በሰሙ ጊዜ
ግን ሁለቱም ደነገጡና ወደቁ መልአኩ
ሩፋኤልም ፈጣሪያችሁ እግዚአብሔርን
ፍሩት እንጂ እኔን አትፍሩኝ የፈጣሪያ
ችሁ ፈቃድ አመጣኝ እንጂበራሴ ፈቃድ
አልመጣሁም ስለዚህም ምስጋና ለእግ
ዚአብሔር ነው እንጂ ለእኔ አይገባኝም
በዘመናችሁም ሁሉ እግዚአብሔርን
አመስግኑ ፡፡

እኔ ግን ተገለጥሁላችሁ መልኬንም
አያችሁ ከእናንተ ጋር አልበላሁም አል
ጠጣሁም ወደላከኝ ወደ እግዚአብሔር
እወጣለሁና አሁንም በእግዚአብሔር
እመኑ በላከውም መልአክ እመኑ ብሎ
ነግሯቸው መልአኩ ሩፋኤል ከጦቢትና
ከጦብያ ተለይቷል ፡፡

ቅዱስ ሩፋኤል በሰው አምሳል ቀርቦ
ስሙንም በሰው ስም አዛርያ ብሎ ሰይ
ሞ ለጦቢት የተላከውና ያገለገለው
ጦቢት እግዚአብሔርን ፈሪ ፣ ትእዛዙን
ፈጻሚ ፣ ሕጉንም አክባሪ ሆኖ በመገኘቱ
ነው ሁላችንም በእግዚአብሔር አምነን
ሕጉን አክብረን ትእዛዙን ጠብቀን
ከኖርን ችግር በደረሰብን ጊዜ እንደጦቢ
ት ብንለምነው እግዚአብሔር ልመናች
ን ሰምቶ ቅዱስ ሩፋኤልንና ሌሎችንም
መላእክት ለተራድኦ ይልክልናል ፡፡

ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

## ቤተ ክርስቲያንና ኅብረተ ሰብእ

ከገጽ ፰ የዞረ

ማኅታዊ ጥበብን አገናዝቦ ማወቅ ታላ
ቅ ብልህነት ነው ፡፡ አንድ ሊቅ እንዲህ
ሲል ተናግሮአል ፡፡ ሰብአዊ ተፈጥሮም
ግብረ ገብነትንና መንፈሳዊ ልደትን
እጅግ በጣም የሚያስፈልገው ሁኖ ይታ
ያል ፣ እሱም በሃይማኖት መንፈስ አዲ
ስ ሕይወትን ለማግኘት መጣጣር ነው፡፡

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው ቤተ ክርስ
ቲያን ለሞራልና ለሃይማኖት ጥያቄዎች
መልስ ትሰጣለች ብለናል ፡፡ ለምሳሌ የ
ኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክ
ርስቲያን ከቀድሞ ጀምራ የትንባሆ ቅ
ጠል ወይም በዛሬው አነጋገር ሲጋሬት
ማጤስ ለሰዎች መጥፎ ነው እያለች ስ
ታስተምር ኑራለች ፡፡ ይህም ሊሆን የቻ
ለበት ምክንያት ኅብረተሰብኡ አደገኛ
በሆኑ የዕፅዋት ቅመማት እንዳይመረዝ
አእምሮውም እንዳይደነዝዝና ትውል
ዱ የጤንነት መዛባትና የሞራል ውድቀ
ት እንዳይደርስበት አርቆ በማሰብ ሲሆ
ን ፣ ይህም የግብረገብ ወይም የሞራል
ትምህርት እንጂ ትምህርተ መለኮት ወ
ይም የሃይማኖት ዶክትሪን አይደለም ፡፡
ሲጋሬት ያጤሰ ወደ እግዚአብሔር መን
ግሥት አይገባም ወይም ይኰነናል በማ
ለት ብቻ ሳይሆን የኅብረተሰብኡን የጤ
ንነትና የሞራል አቅዋም ለመጠበቅ ጭ
ምር ነው ፡፡

በመጽሔቶችና በጋዜጦች ዘወትር
እንደምናነበው መንግሥትም የዕፁን አ
ደገኛነት በመረዳት በሕክምና ሊቃው
ንት አማካኝነት ለኅብረተሰብኡ ትምህ
ርት እንዲሰጥ ያደርጋል ስለዚህ ሞራሉ
የጠነከረ ፣ ሃይማኖቱ የጸና ፣ ጤንነቱ የ
ተጠበቀ ትውልድ ለማፍራት መንግሥ
ት እንደአካል ፣ ቤተ ክርስቲያን እንደ
ነፍስ ሁነው ይሠራሉ ፣ ቤተ ክርስቲያ
ን የሁሉ ናትና ፡፡





www.ethiopianorthodox.org

# የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት

የአፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት የልማት አስተዋጽኦ ኅብረት እኤአ በጥቅምት ወር ፲፱፻፺ በሴራሊዮን ርዕሰ ከተማ በፍሪታውን ባደረገው ስብሰባ በየአገሮቻቸው የሚገኙት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በኢኮኖሚና በሰው ልጆች መብት ላይ ያደረሱትን በደልና በቤተ ክርስቲያንም ሐዋርያዊ ተግባር ላይ ያሳደሩትን ተጽእና አብሮ ጐን ለጐን በዝርዝር እንዲጠና ባሳለፈው ውሳኔ መሠረት ፣ በጥናቱ ላይ ለመነጋገር ተከታዩ ስብሰባ እኤአ ከመስከረም ፪ እስከ ፯ ፲፱፻፺፩ በቶጐ ርእሰ ከተማ በሎሜ እንደተደረገ ይታወሳል ።

በ፲፱፻፺፩ ስብሰባ ላይ ሁለት ዝርዝር ጥናቶችና ማለትም ድንበር ዘለል ኩባንያዎችና የዘመናዊ ቴክኖሎጂ መስፋፋት የቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊነትና ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች በሚሉ ርእሶች ሲቀርቡ ሶስት ሰዎች ደግሞ የድንበር ዘለል ኩባንያዎች አቋምና እንቅስቃሴ ፣ ድንበር ዘለል ኩባንያዎችና የእርሻ ልማት በአፍሪካ ፣ በኬንያ የሚገኙ የዓለም አቀፍ ኩባንያዎች አቋም በሚሉ ርእሶች ሪፖርት አሰምተዋል ። ከጉባኤውም ተሳታፊዎች በየአገሮቻቸው ስለሚገኙት ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ልዩ ልዩ አስተያየቶች ቀርበዋል ።

የድንበር ዘለል ኩባንያዎች ሕገወጥ ዕድገትና በአፍሪካ ማበባቸው ፣ የአብያተ ክርስቲያናት ኃላፊነት በአፍሪካ በሚሉ ርእሶች ጥናቶቹን ለአንባብያን ብናቀርብ የጉባኤውን መንፈስ ከመረዳታቸውም በላይ ስለእነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በይበልጥ እንደሚረዱልን እናምናለን ።

ሕገወጥ ዕድገታቸውና ማበባቸው

እኤአ እስከ ፲፱፻፷ ዓ.ም. ድረስ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ቅኝ ግዛቶች እንደነበሩ ይታወሳል ። የአፍሪካ ምድር ደግሞ በማዕድንና በሌሎችም የተፈጥሮ ሀብት የበለጸገች በመሆኗ ለአውሮፓ እንዱስትሪዎችና ፋብሪካዎች የጥሬ ዕቃዎች ምንጭ በመሆን አሁንም በማገልገል ላይ ትገኛለች ። አውሮፓውያንም የደለበውን ሀብት የሚጋፍፉባቸው ልዩ ልዩ ኩባንያዎች አቋቁመው ነበር ። የእነዚህ አነስተኛ ኩባንያዎች ዕድገት ከጊዜ በኋላ ከእነርሱ ላቀና ሰፋ ያሉትን ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ሊወልድ ቻለ ። እነዚህም ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ማዕድናትን በመፈለግና በመቆፈር ብቻ ሳይወሰኑ በፋብሪካ ማምረትና - ሸቀጣሸቀጥ ማከፋፈልን - አልፈው ተርፈውም የእርሻውን ክፍል ኢኮኖሚም የመቆጣጠሩን ተግባር ተያያዙት ከላይ እንደተገለጸው ምንም እንኳን እኤአ ከ፲፱፻፷ ዓ.ም. ወዲህ አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ነፃነታቸውን የተጐናጸፉ ቢሆንም ቅሉ ፣ ቅኝ ገዥዎቹ በእነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ያላቸውን የባለቤትነት ድርሻም ሆነ ሥልጣን የአመራር ልምድ ከአዲሶቹ ነፃ አገሮች የፖለቲካና የኢኮኖሚ መዋቅር ጋር ለማዛመድ ፈቃደኞች ሆነው አልተገኙም ። በሌላ አንጻር ደግሞ አንዳንዶቹ የነፃዎቹ አገሮች ባለሥልጣኖች መሪዎች እንዲሁም የመንፈሳዊ መሪዎችም ጭምር አገሮቻቸው የሠለጠኑላቸውና የውጭ ካፒታልም የሳቡ መስሏቸው የድንበር ዘለል ኩባንያዎች ጥቅም ተካፋይ በመሆናቸው አፍሪካን ለብዝበዛ አጋልጠው ከመስጠታቸውም በላይ የባዕድ እጅ ቁጥጥር እየተባባሰ እንዲሄድም ተባብረዋል ። ሁኔታዎችን ለማብራራት ያህል ምሳሌዎችን ብንጠቅስ ።

ሀ/ እኤአ በ፲፱፻፸፫ ክርስታቸው ከተባረሩት ኢትዮጵያውያን እርሻ ላይ "ማኤስኮ" የሚባለው የኢጣልያን ኩባንያ በጃፓን ለሚገኙ የቀንድ ከብቶች "አልፋ አልፋ" የሚባል ሣር ዘርቶ በሚያገኘው የመና ገቢ እየተንሰራፋ ሲሄድ ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን ግን በረሃብ አለንጋ እያለቁ ነበር ።

ለ/ አይቢኤምና አይሲኤል የሚባሉ የኮምፒውተር ኩባንያዎች ኮምፒውተሮቻቸውን ለደቡብ አፍሪካ የነጮች መንግሥት በመሸጣቸው የአገሬው እውነተኛ ሕዝብ ማለት ጥቁሮቹ የሚጠሉትን የይለፍ ወረቀት ተገድደው እንዲይዙ ለጥቁሮቹ የሚከፈለውም ደመወዝ የዕለት ጉሮሮ ለመዝጋት ያህል ብቻ ተወስኖ እንዲቀርና አፓርታይድ እንዲሠፍን ረድተዋል ።

በሌሎቹም የአፍሪካ አገሮች ላይ የሚፈጸመውን በደል በዝርዝር ለማቅረብ ቢቻልም ቅሉ ጊዜና ቦታ ስለማይፈቅድልን በዚሁ አብቅተን በአቅጣጫው ደግሞ የቤተ ክርስቲያንን ኃላፊነትና ተሳትፎ እንመለከታለን ።

በጉባኤው ተሳታፊዎች ቤተ ክርስቲያን ስለ እነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች እንቅስቃሴ የምታውቀው ነገር እጅግም መሆኑን ለመገንዘብ ቢቻልም ቅሉ በደል ሲፈጸም ዝም ብላ ከተመለከተች ኃላፊነቷን የዘነጋች ስለሚመስል ከመወቀስ አያድናትም ። ይሁንና የኩባንያዎቹ ሤራ እንዳይታወቅም ምክንያት የሆኑት ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው ።

- ኅብረተሰቡ የኢኮኖሚው አውታርና ምሰሶዎች ናቸው ብሎ እንዲያምንባቸው የሚያደርጉት ቅስቀሳ
- ኩባንያዎቹ ለቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉት የይስሙላ ዕርዳታ
- የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኩባንያዎቹ ውስጥ ባለአክሲዮንና የቦርድ አባላት መሆን

ኩባንያዎቹ ያደረሱትን ጥፋት አውቀው ሆነ ሳያውቁ ተሸፋፍኖ እንዲቀር በጉልህ መርዳታቸው ይታመናል ። በሌላ በኩል ደግሞ አንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት የመንፈሳዊ ትምህርት ተቋሞች ስለእነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በደል ያጠኑና በማጥናትም ስላሉ የጥናቱን መንፈስ ማቅረብ እንደሚበጅ ስለሚታመንበት ጥናቱ እነሆ ።

፩ - ብሔራዊው የኬንያ ክርስቲያኖች ምክር ቤት (ኤንሲሲኬ) በኬንያ የሚገኙ ኩባንያዎች ባለቤት (ሃብት) ማንነው በሚል ርእስ በሚያቀርባቸው ጽሑፎች ሕዝቡን እያነቃ ነው ።

፪ - በቀድሞው የምሥራቅ አፍሪካ ኅብረት ውስጥ የሚገኙ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች በእነዚህ አገሮች ኢኮኖሚ ላይ ምን ዓይነት ሚና ይጫወቱ እንደነበር የአፍሪካ ክፍል የዓለም ክርስቲያን ተማሪዎች ፌዴሬሽን ዩአርኤም ያቀረቡት ረቂቅ

፫ - ኢባዳን በሚባለው የናይጄሪያ ከተማ የሚገኘው የመንፈሳዊ ትምህርት ማዕከል ባለፉት ሶስት የአገሪቱ የልማት ፕላን ዓመታት ውስጥ እነዚህ ድንበር ዘለል ኩባንያዎች ምን ጥቅምና ጉዳት እንዳደረሱ የሚያካሂደው ጥናት

፬ - በሴራሊዮን ኢኮኖሚም ላይ ምን በደል እንደፈጸሙ የሚደረገው ግምገማ

፭ - እንዲሁም የጋና የክርስቲያኖች መማክርት ጉባኤ የአገሪቱ ኢኮኖሚ እንዴት ኰታኰት የገፋፉትና የፈጸሙትን በደል ለማጥናት የወሰደው ርምጃና ጥናት

፮ - በካሜሩንም ውስጥ ዩኒሌቨር የፈጸመው በደል

፯ - አብያተ ክርስቲያናት በልማት ተሳታፊ በሆኑባቸው ሌሎች አገሮች ደግሞ እነዚህ ኩባንያዎች በሰው ሕይወት ላይ ምን ያህል ተጽእኖ ያሳድሩ እንደነበር የተጠናቀቀው ምርመራ

እንዲህ ያሉት ርምጃዎች የሚያበረታቱና በጉባኤው ተሳታፊዎችም ዘንድ ተቀባይነት ያገኙ ቢሆንም ቅሉ በቂ ሆነው ባለመገኘታቸው ስለድንበር ዘለል ኩባንያዎች እንቅስቃሴ በአገር በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ሰፋ ያለና ጠለቅ ያለ ጥናት እንዲያካሂድ በተወሰነው መሠረት መወሰድ ስለሚገባቸው ርምጃዎች ከጉባኤው የተሰጠው የመመሪያ ሐሳብ የሚከተለው ነው ። ጉባኤው በአገርና በአህጉር ደረጃ ካወጣቸው ሰባት ሰባት አንቀጾች ለዚህ መልእክት ብቻ ከሁለቱም ክፍል ሶስት ሶስቱን እናቀርባለን ።

ሀ- በአገር ደረጃ

- እያንዳንዱ አገር ስለነዚህ ኩባንያዎች እንቅስቃሴ መረጃዎችን በመሰብሰብ ያገኘውን ልምድና ጥናት መለዋወጥ
- የወጣቱን የሠራተኛውን የገበሬውን የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችንና የአባቶችን እንዲሁም የአገር መሪዎችን በአጠቃላይም የኅብረተሰቡን ንቃተ ሕሊና ከፍ ለማድረግ ትምህርታዊ ሰሚናሮችን መስጠት ፣ በልዩ ልዩ የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችም ማስተማር
- በሴራሊዮን በታንዛኒያና በናይጀሪያ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ሕዝቡን ለማሠልጠን የዘረጓቸውን የልማት እቅዶችን ለማስፈጸምም የወሰዷቸውን ርምጃዎችን በማጥናት የተሻለና የበለጠ የልማት እቅድ ማዘጋጀትና መዘርጋት

ለ - በአህጉር ደረጃ

- አስተሳሰብንና የአሠራርን ልምድ ለማሻሻል ሰፋም እንዲል በሌሎች አህጉር የተጠኑትንና በተለይም አፍሪካን በሚመለከት ረገድ ከልዩ ልዩ አቅጣጫ የቀረቡትን ሪፖርቶች ማጥናት
- በኅብረተሰቡ ዘንድ ቀድሞ የነበራቸውን ለማስቀረትና መሠሪ የጥቅም ማጋበሻ ዘዴዎቻቸውን ለማክሸፍ ሕዝባዊ አስተያየቶችን የሚቀበልና የሚያስተጋባ ድርጅት ማቋቋም
- እነዚህ ኩባንያዎች በአፍሪካ ውስጥ እንዴት ሊበዙ እንደቻሉ የሚያሳዩ ሥዕላውያን መግለጫዎች በማዘጋጀት ሕዝቡን ማስተማር ።

ሐ - በዓለም አብያተ ክርስቲያናት የማምክርት ጉባኤ ደረጃ

- የአፍሪካን ሕዝብ ንቃተ ሕሊና ከፍ ለማድረግና የቤተ ክርስቲያንን ሐዋርያዊ ተልእኮ ለማጠናከር ባወጣው እቅድ መሠረት የሚያዘጋጃቸው መጽሔቶች ጠቃሚነታቸው የተረጋገጠ ቢሆንም ቅሉ በስፋትና በጥልቀት እንዲቀርቡ ማድረግ
- ሕዝቡ የሚያውቀውና ሊረዳው በሚችለው ቋንቋዎች መጽሔቱን ማዘጋጀት
- የእነዚህን ኩባንያዎች ኃይል ለመቋቋም የጥናት ሐሳብ ልውውጥ እንዲደረግ በአህጉር መካከል ኅብረትና አንድነት እንዲኖርና በተለይም የአፍሪካ አገሮች እርስ በርሳቸው እንዲተባበሩ ማድረግ
- የየዘመኑን የዓለምን ሁኔታ በመመልከትና በማጤን እኩልነት ሰላምና ፍትሕ የሰፈነበት እንዲሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ የሚቻለውን ሁሉ ከማድረግ እንዳይቆጠብ የሚሉ የመንደርደሪያ ሐሳቦችን አቅርበዋል ።

ከላይ ከቀረቡት ሪፖርቶች አስተያየቶችና የመመሪያ ሐሳቦች ለመረዳት እንደሚቻለው ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን ማስተማር ትታ ነጋዴ ለመሆን በመተናነቋ ልጆቿን በተኩላ ማስነጠቋን እንመለከታለን ።

ሁኔታዎችን ወደ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን እንመለሰውና አንዳንድ ጥያቄዎችን እናቅርብ ። ቅጭል ቅጭል ለሚለው የሣንቲም ድምፅ በሩን ከፍታለችን ? "ቤቴ የጸሎት ቤት ነው" የሚለውን መለኮታዊ ትእዛዝ ዘንግታው ይሆንን ? በአጭሩ ለገንዘብ ያልተገዛችነችን ? እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎች በማስፈርና ለቤተ ክርስቲያን ጽናት ይረዳሉ ብለን የገመትናቸውን ሶስት አጫጭር ሁኔታዎች እንተርክ

፩ - የሕፃናትን የአመጋገብና የአስተዳደግ ሁኔታ በሚቆጣጠረው "ኢንፋክት" በተባለው ክርስቲያናዊ ድርጅትና "ኔስል" በሚባለው የቆርቆሮ ወተት አምራች በሆነው ኩባንያ መካከል የተደረገውን የፍትሕ ግብግብ በአጭሩ እንመልከት ። ምንም እንኳን የእናትን ጡት የሚተካ የቆርቆሮ ወተት ለማዘጋጀት ያልተቻለ መሆኑ ቢታወቅም ቅሉ ኩባንያው ምርቱን ለማስተዋወቅ ካዘጋጃቸው ማስታወቂያዎች አንዱ "የእናትን ጡት የሚተካ" የሚል ማስታወቂያ በዜና ማሰራጫዎች በማቅረቡ ኢንፋክት ጽኑ ተቃውሞውን እንዲያቀርብ ተገደደ ። ተቃውሞ ማቅረብ ብቻ ሳይሆን በአያሌ አብያተ ክርስቲያናትም

ወደ ገጽ ፲፭ ዞሯል





www.ethiopianorthodox.org

# ትምህርተ ግእዝ　ትምህርት ፱　የግእዝ ትምህርት

## አንቀጸ ሀልዎ (የመኖር ግሥ)

"ቦ" አለ ነበረ

መክሥት ፤ "ቦ" የተሰኘው የመኖር አንቀጽ በመጀመሪያ ምንም ሳይለወጥ በአሥሩ መራህያን ይረባል ።

አምሳል ፦ ቦ ፤ አለሁ ፤ አለህ ፤ አለሽ ፤ አለ ፤ አለች ።
ቦ ፤ አለን ፤ አላችሁ (ተባ - አን) አሉ (ተባ - አን)

መዘክር ፦ ከዚህ ሌላ ደግሞ ለአንድ ሰው አንድ ነገር እንዳለው ለማመልከት "ቦ" የሚለውን የመኖር ግሥ እንደሚከተለው እናረባለን ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ብየ | አለኝ | ብነ | አለን |
| ብከ | አለህ | ብክሙ (ተባ) | አላችሁ |
| ብኪ | አለሽ | ብክን (አን) | ” |
| ቦቱ | አለው | ቦሙ (ተባ) | አላቸው |
| ባቲ | አላት | ቦን (አን) | ” |

### ለገቢረ ዐረፍተ ነገር

(ዐረፍተ ነገር ለመሥራት) እንድንችል የሚከተሉትን ቃላት እናጥና ።

#### ቃላት

| | | | |
|---|---|---|---|
| መሐፒል | ሳሙና | መጽሔት | መስታዋት |
| ማሕደፍ | ፎጣ | መጥባሕት | ቢላዋ |
| ማሕው | ብርጭቆ | መሐሥሥ | ሹካ |
| መሥዕርት | ሚዶ | ኑ | ቃለ ተስእሎ |

#### ዐረፍተ ነገር

| | |
|---|---|
| ቦኑ መምህር | አስተማሪው አለን ? |
| እወ ቦ መምህር | አዎ አስተማሪው አለ |
| ቦኑ እምከ ውስተ ቤት | እናትህ በቤት አለች ? |
| ቦኑ መሐፒል | ሳሙና አለወይ ? |
| እወ ቦ መሐፒል | አዎ ሳሙና አለ |
| ብከኑ ማሕደፍ | ፎጣ አለህን |
| እወ ብየ ማኅደፍ | አዎ ፎጣ አለኝ |
| ብኪኑ መጽሔት | መስታዎት አለሽን ? |
| ምንት ብክሙ (ተባ) | ምን አላችሁ ? |
| ብነ ንዋይ | ገንዘብ አለን |
| ምንት ብክን (አን) | ምን አላችሁ ? |
| ብነ ኵሉ ነገር | ሁሉ ነገር አለን |

#### መዘክር

"ቦ" የሚለውን የአዎንታ አንቀጽ ወደ አሉታ ለመለወጥ "አል" የሚል ቃል እንጨምራለን ።

ይህንም አሁን እንማራለን ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| አልቦ | የለም | አልብነ | የለንም |
| አልብየ | የለኝም | አልብክሙ (ተባ) | የላችሁም |
| አልብከ | የለህም | አልብክን (አን) | የላችሁም |
| አልብኪ | የለሽም | አልቦሙ (ተባ) | የላቸውም |
| አልቦቱ | የለውም | አልቦን (አን) | የላቸውም |
| አልባቲ | የላትም | | |

ግብረ ቤት በ"ቦ" የሠራችሁትን ዐረፍተ ነገር "አልቦቱ" በሚለው አንቀጽ ለመሥራት ሞክሩ ።





ወጣቶች በቤተ ክርስቲያን

በወጣትነትህ ወራት ፈጣሪህን አስብ (መክ. 12-1)

አዘጋጅ ኢሳይያስ ወንድምአገኘሁ

## ወጣቶች በጾመ ፍልሰታ

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ሰባት አጽዋማት ያሉ ሲሆን ከነዚህ አንደኛው ስለእመቤታችን ፍቅርና ስለእሷም መታሰቢያ በየዓመቱ ከነሐሴ አንድ እስከ ፲፭ ቀን የሚጾመው የፍልሰታ ጾም ነው ። በጾመ ፍልሰታ ሽማግሌዎች ማዕከላውያን ሰዎችና ወጣቶች እንዲሁ ሕፃናት ጭምር በመተባበር በጥንቃቄ ሲጾሙ ይታያሉ ። ይልቁንም ወጣቶችና ሕፃናት በዚህ በፍልሰታ ጾም ወቅት የሚያሳዩት መንፈሳዊ እንቅስቃሴና የጾም ሥነ ሥርዓት እጅግ የሚያስደስትና ወጣቱ በእምነት በኩል መልካም አዝማሚያ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጥ ነው ።

በጾመ ፍልሰታ ጾማቸውን ውለው በየቤተ ክርስቲያኑ የሚያስቀድሱትን ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉትን ወጣቶች ብዛት የሚያይ ሁሉ ከሌሎቹ አጽዋማት ይልቅ በፍልሰታ ጾም ወጣቶችና ሕፃናት እንዴት የበለጠ ሊጾሙና ያለማቋረጥ ሊያስቀድሱ ቻሉ ? እንዴትስ ለሥጋ ወደሙ ዝግጁ ሆነው በዚህ ጾም ውስጥ ቅዱስ ቁርባንን ይቀበሉ ዘንድ ለመሽቀዳደም በቁ ? የሚል ጥያቄ በአእምሮው ይጉላላ ይሆናል ። መልሱ ግን የሚከተለው እንደሚሆን ተስፋ እናደርጋለን ።

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አማኞች በእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም አማላጅነት አጥብቀው ስለሚያምኑ ሁልጊዜ በርስዋ ይማጸናሉ ። ስለፍቅራቸውም የእመቤታችንን ስም ጠርቶ ለሚለምናቸው ሁሉ መዘከር ደስ እንደሚላቸው ሁሉ የእሷም መታሰቢያ ሆኖ የሚጾመውን የፍልሰታ ጾም በመጾምና በዚህ ጾም ሱባኤ ገብተው በእሷ አማላጅነት ተማጽነው ጌታን ቢለምኑት ኃጢአታቸው እንደሚሠረይላቸው በማመን ይህን ጾም በጥንቃቄ ይጾሙታል ። ከዚህም የተነሣ ቤተሰባቸው ሁሉ ይህን ጾም ቢጾሙ ዋጋ ያገኛሉ ብለው ስለሚያምኑ ወላጆች ልጆቻቸው እንዲጾሙ ያበረታቷቸዋል ። በዚህም ምክንያት ብዙዎች ወጣቶች አባት እናታቸውን በማየትና በመመልከት እነሱም የእመቤታችን ፍቅር እያደረባቸው በብዛት ሲጾሙና ሥጋ ወደሙን ሲቀበሉ ይታያሉ ።

፪. የጾሙ ጊዜ አጭርነት ነው ። ዓቢይ ጾም ሁለት ወራት ያህል እንደሚጾም እናውቃለን ። ይህም ስምንት ሱባኤ መሆኑ ነው ። ይህ ጊዜ በጣም ረጅም ከመሆኑም የተነሣ እንኳን ለሕፃናት ለአዋቂዎች ወደመሰልቸቱ ደረጃ ሊያደርሳቸው ስለሚችል አብዛኞዎቹ በፍልሰታ ጾም የሚያደርጉትን ጥንቃቄ ያህል ተጠንቅቀው ሱባኤውን ላይፈጽሙት ይችሉ ይሆናል የፍልሰታ ጾም ግን ሁለት ሱባኤ ብቻ በመሆኗ በነዚህ ፲፭ ቀናት ውስጥ የሚጾሙት ጾምና የሚገቡት ሱባኤ ሁሉ በቀላሉ የሚፈጸም በመሆኑ ያለመሰልቸት ተጠንቅቀው ይጾሙታል እነሱም ብቻ ሳይሆኑ ልጆቻቸውም ጭምር በዚህ አጭር የጾም ጊዜ ውስጥ ራሳቸውን በጾም ፈትነው ይኸውም መለማመጃ ሆኗቸው ለታላቁ ዓቢይ ጾምና ለሌሎቹም አጽዋማት እንዲዘጋጁ ስለሚያደርጓቸው በዚሁ ልምድ መሠረት ወጣቶችና ሕፃናት በይበልጥ በጾመ ፍልሰታ ሲጾሙ ይታያሉ ። ስለሆነም ዕድሜያቸው ከ፯ እስከ ፲፭ ዓመትና ከዚያም በላይ በብዛት በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲያበረክቱ ይታያሉ ።

፫. ወቅቱ ትምህርት ቤት የሚዘጋበት በመሆኑ በተለይ በከተማ የሚገኙ ወጣቶች ለዚህ መንፈሳዊ አገልግሎት ምቹ ጊዜ በማግኘታቸው ነው ።

ሌሎቹ የጾም ጊዜዎች የትምህርት ወቅቶች በመሆናቸው ወጣቶቹ ቁርሳቸውን ሳይበሉ ወደትምህርት ቤት መሄድ ከዚያም ተመልሰው ለማስቀደስና መንፈሳዊ አገልግሎት ለመፈጸም ምቹ ጊዜ ስለማይሆንላቸው ከሌሎቹ ይልቅ ጾመ ፍልሰታ ከጊዜው ዕጥረትና ከእረፍት ጊዜያቸው ጋር ካለው ሁኔታ ጋር ሲዛመድ በሁሉም አመቺ ጊዜ ስለሚሆንላቸው ወጣቶች ሁሉ በዚህ ጾም ይተባበራሉ ከዚህ የተነሣ በአዲስ አበባ ውስጥ



www.ethiopianorthodox.org

ካሉት አድባራት በአብዛኛዎቹ ተዘዋውረን እንደተመለከትነው በጾመ ፍልሰታ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚያስቀድሱት ወጣቶችና ሕፃናት ቁጥር በብዙ ሺህ የሚቆጠር ነው ። ስለሆነም በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናት በየቀኑ ከአንድ ሺ በላይ የሚሆኑ ወጣቶች የሚቆርቡበት ጊዜ አለ ። ከዚህም የተነሣ ቤተ ክርስቲያኑ እንዳይጠብ በውጭ ይሰለፋሉ ያም ሴቶቹና ወንዶቹ እንዲሁም ሕፃናቱ በፕሮግራም ተለይተው በተለያዩ ቀናት እንዲቆርቡ በመሆኑ ነው ።

ወጣቶች በጾመ ፍልሰታ የሚያከሂዱት መንፈሳዊ አገልግሎት መጾምና መቁረብ ብቻ ሳይሆን መንፈሳዊ ትምህርት በመማርና ያወቁትንም ለሌሎች በማስተማር ረገድ ሰፋ ያለ አገልግሎት ይሰጣሉ ለዚህም መንፈሳዊ ሥራ የሰንበት ት/ቤት መንፈሳውያን ወጣቶች ግምባር ቀደሞች ናቸው ። ስለዚህ ሁኔታ በአለፉት ዓመታት በየቤተ ክርስቲያኑ የተከናወኑትን መንፈሳውያን እንቅስቃሴዎች በየወቅቱ የገለጥን ቢሆንም በዘንድሮው ዓመትም ምን ዕቅድና ፕሮግራም እንዳለ ልናውቅ ፈልገን ለመንፈሳውያን ማሕበራት አንጋፋ የሆነው የማሕበረ ክርስቶስ ዘመንበረ ፀባዖት ቅ.ሥላሴ ወጣቶች መንፈሳዊ ማኅበር በዘንድሮው የፍልሰታ ጾም ምን ፕሮግራም አዘጋጅቷል የሚል ጥያቄ አቅርበን ነበር ።

የማኅበሩ ዋና ጸሐፊ ዲያቆን ወሰን ሰገድ ብርሃኑ ለዚህ ጥያቄ በሰጠው መልስ "ማኅበሩ ባለፉት ዓመታት እንደሚያደርገው ሁሉ በዘንድሮውም ዓመት ጾመ ፍልሰታን እየጾሙ ለማስቀደስና ለመቁረብ የሚመጡትን ወጣቶችና ሕፃናት ከሁለት በመክፈልና በመመደብ ከ፲፪ ዓመት በላይ ያሉትን በቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ አስቀድሰው በዚያው ሥነ ሥርዓታቸውን ጠብቀው እንዲቆርቡ ለማድረግና ከ፭ እስከ ፲፪ ዓመት ባለው ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት ግን አብዛኛዎቹ ሕፃናት በመሆናቸው በቅዳሴ ጊዜ እንዳይንጫጩና ሥነ ሥርዓት እንዳያበላሹ በማሰብ በቀጥታ ወደ አዳራሽ ገብተው ፦

፩ኛ/ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት በዓቅማቸው መጠን

፪ኛ/ ቅዱስ ቁርባን የሚሰጣቸውን ጥቅም

፫ኛ/ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን

፬ኛ/ ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበላቸው በፊትና ከተቀበሉም በኋላ ሊያደርጉት ስለሚገባቸው ጥንቃቄ ።

፭ኛ/ አእምሯቸው ይታደስ ዘንድ መንፈሳዊ መዝሙር እያጠኑ ይቆዩና ጸሎተ ቅዳሴው ተካሂዶ እግዚኦ በሚባልበት ጊዜ በሰልፍ ወደ ቤተ ክርስቲያን ገብተው ሥጋ ወደሙን እንዲቀበሉ እናደርጋለን" በማለት አብራርቷል ።

ዲያቆን ወሰን ሰገድ ከ፲፪ ዓመት ዕድሜ በላይ ላሉት ወጣቶች በይበልጥ በቤተ ክርስቲያን ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከቅዳሴ በፊት ልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት እንዲያጠኑ ማኅበሩ ፕሮግራም ያዘጋጀ መሆኑን ገልጦ ይህም ፕሮግራም የሚካሄደው በማኅበሩ መንፈሳውያን ወጣቶች መሆኑን አስገንዝቧል። ቀጥሎም ዲያቆን ወሰን ሰገድ በሰጠው ማብራሪያ እንደተገነዘብነውና እኛም ሁልጊዜ እንደምናየው የማኅበረ ክርስቶስ ዘመንበረ ፀባዖት ቅ.ሥላሴ መንፈሳውያን ወጣቶች አገልግሎታቸውን የሚያበረክቱት በተለያየ አግጣጫ ነው ።

ለምሳሌ ፦ የዲቁና ማዕረግ ያላቸው ወንጌል በማሳለም የቅዳሴ ጠበል ቡ[illegible]ስ ጠትና ምእመናንን በማስተናበር ሲያገለግሉ ሌሎቹ ደግሞ መዝሙር በመዘመር የቅዳሴ ተሰጥዎ በመቀበልና በመሳሰለው መንፈሳዊ ተሳትፎ ያደርጋሉ ። ይህም በአዳራሹ ውስጥ ሕፃናቱን በማስተናገድ ከሚሰጡት አገልግሎት ሌላ ነው ።

ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ረገድ ግን የማኅበሩ ወጣቶች የሚቆርቡት በጾመ ፍልሰታ ብቻ ሳይሆን እንደልደት ጥምቀትና - ትንሣኤ ባሉት ዓበይት በዓላት ጭምር ሥጋ ወደሙን እየተቀበሉ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን የሚያጠናክሩ መሆናቸውን ለመረዳት ችለናል በሌሎቹ አድባራትስ እንዴት ይሆን ? በአለፉት ዓመታት የጾመ ፍልሰታ የስብከተ ወንጌል ሥምሪት ወቅት በየአድባራቱ ተዘዋውረን እንዳየነውና በደረሰንም ሪፖርት መሠረት በብዙ ቦታዎች ያሉት ወጣቶች ተመሳሳይ አገልግሎት እየፈጸሙ የሚገኙ መሆናቸውን በመገንዘባችን አሁንም በዚሁ ይቀጥሉ እንላለን ።

## ደብዳቤዎች

ለትንሣኤ መጽሔት

አ.አ.

ሁለት ጥያቄዎች አሉኝ ፦

ማንኛውም የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ተከታይ የሆነ ሁሉ ስለ ሃይማኖቱ የሚያስረዳውን መጽሐፍ እየተከታተለ ካነበበ ከማንኛውም ሕገ ወጥ ተግባር ተወግዶ የፈጣሪውን ትእዛዝና የቤተ ክርስቲያኑን ሕግ በሚገባ ጠብቆ ለመኖርና የማታልፈውን መንግሥተ ሰማያት ለመውረስ ይችላል ።

ይሁንና እኔ እንደ ሐዋርያት መልካም ተግባር አይኑረኝ እንጂ እኔን የሚመለከተኝን ከማንኛውም. አስፀያፊ ተግባር የሚመልሰኝና እኔም ተመልሼ ሌላውንም በማስተማር ለመመለስ አንዳንድ መጻሕፍትን ስከታተል ፣ መጽሐፎች በቃላት የተለያዩ እንዳይሆኑ ታርመው የወጡ ሲሆን አንዳንዶቹ ምእመናንን ግራ የሚያጋባ ጽሑፍ አዝለው የሚታዩ መስለውኛል ።

እነዚሁም የተለያዩ ሐሳቦች ካገኘሁባቸው መጻሕፍት ልዩነታቸውን በመጥቀስ ጠይቄ ለመረዳት አቅርቤአለሁ ።

፩ኛ/ መርሐ ጽድቅ ባህለ ሃይማኖት የሚለው ከሊቀ መዘምራን ሞገስ ዕቁበ ጊዮርጊስ የተዘጋጀው "ሥርዓተ ቁርባን" በሚለው ርዕስ ላይ ቆራብያኖች ምን ሰዓት ተመግበው ስንት ሰዓት መጾምና መቁረብ እንደሚገባቸው አብራርቶ ከገለጸ በኋላ እስከ 18 ሰዓት መጾም ያለበት መሆኑን ማስረጃ ሲያቀርብ ጌታ ከሌሊቱ ፱(ዘጠኝ)ሰዓት ከቀኑ ፱(ዘጠኝ )

ተከታዩ ወደ ገጽ ፳፱ ዞሯል



# "ከሕግ ለወጡ ሰላም የላቸውም"

ሕግና ሰላም ጐን ለጐን የሚራመዱ ጓደኛሞች ናቸው ሕግ በሚጠበቅበት ሰላም ይሰፍናል ሰላምም በሚሰፍንበት አካባቢ ሕግ ይጠበቃል ሕግ ከሌለ ደግሞ ሰላም አይኖርምና ጥላቻ ጠብ ክርክር የመሳሰሉትም የሰላም ጠንቆች ይበረክታሉ ።

እግዚአብሔር አምላካችን የሰላምና የሕግ ባለቤት በመሆኑ ሁለቱም እንዲጠበቁ አምላካዊ ፈቃዱ ነው የመጀመሪያዎችን ሰዎች ፈጥሮ ያለ ሕግ አልተዋቸውም ሰላምን ሰጥቶ ሕግን ሰርቶ በምድረ ገነት ያለ አንዳች ችግር በሰላም እንዲኖሩ አዝዟቸው ነበር ።

በሕጉም ላይ ሁለት እንጨቶችን ፈጥሮ የአንዱን እንጨት ፍሬ ለቅመው እንዲመገቡ ሲፈቅድላቸው የአንዱን እንጨት ፍሬ ግን ቀጥፈው እንዳይቀምሱ በጥብቅ አዝዟቸዋል ተደፋፍረው ቢመገቡ ግን በሕግ አፍራሽነት ተይዘው ከሰላማዊ ኑሯቸው ተፈናቅለው ከምድረ ገነት ተባረው መውጣት እንዳለባቸው አስጠንቀቃቸው ።

ሁለቱ ሰዎች አዳምና ሔዋን ግን እግዚአብሔር በሰጣቸው ሕግ አልተጠቀሙበትም ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው ሕግ ከመመራት ይልቅ በገዛ ፈቃዳቸው መመራትን ስለፈለጉ የተሰጣቸውን ሕግ በድፍረት አፍርሰው የተከለከሉትን የእንጨት ፍሬ ቀጥፈው በሉ ። በዚህ ጊዜ በተፈጥሮ የተሰጣቸው ጸጋቸው ተነሣቸውና ሰላምን አጥተው እንዲኖሩባት ከተፈቀደላቸው ካማረችውና ከተዋበችው ምድረ ገነት ወጡ ከወጡም በኋላ በሰላም ለመኖር አልቻሉም ምድራዊ ኑሯቸውን በኃዘንና በልቅሶ ተጋፈጡት የአዳምና የሔዋን ከሕገ እግዚአብሔር ወጥቶ ሰላም ማጣት በመንጸፈ ደይን መውደቅና በእግረ አጋንንት መጠቅጠቅ በእነርሱም ብቻ ተወስኖ አልቀረም ልጆቻቸው የልጅ ልጆቻቸው እስከ ክርስቶስ መወለድ ድረስ የተነሡት ሰዎች ሁሉ በጠቅላላ ሰላምን በማጣት ሲሠቃዩ ኑረዋል ።

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች በሕግ አፍራሽነት ያጡትን ሰላም መልሶ ለመስጠት ሲል ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዷል በዚያች በተወለደባትም ዕለት ሰማያውያን መላእክት ከምድራውያን ሰዎች ጋር በመሆን ሰላም በምድር ብለው እግዚአብሔርን አመስግነዋል ይሁንእንጂ ሰላም ሕግን በመጠበቅና በእግዚአብሔር ቸርነት እንጂ በቃል ብቻ ሊመሠረት ባለመቻሉ መላእክትና ሰዎች በኅብረት ሆነው ባሰሙት የሰላም ጩኸት ሊመሠረት አልቻለም።

ክርስቶስ በመጀመሪያዎቹ ሰዎች ሕገ ወጥነት የጠፋውን ሰላም ለመመለስ በገባው ቃል መሠረት ከተወለደ በኋላ ቀስ በቀስ አድጎ ሠላሳ ዘመን ሲሞላው ተጠምቆ ሲያበቃ ለመላው ዓለም ፍጹም ሰላም የሚገኝበትን ቃል ማስተማር ጀመረ የክርስቶስ ትምህርት ላድማጭ የማይሰለች እጅግ በጣም አስደሳች በመሆኑ ብዙ ሰዎች ትምህርቱን ለማዳመጥ ይጓጉ ነበር ትምህርቱን አዘውትረው ከሚከታተሉት መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ የያዙት ፲፪ቱ ሐዋርያት ፸፪ቱ አርድዕት ፴፮ቱ ቅዱሳት አንስትንበሩ መቶ ሃያ ቤተ ሰቦችም የሚባሉት እነዚህ ናቸው እነርሱም ክርስቶስ በዋለበት እየዋሉ ባደረበት እያደሩ ቃሉን ያጠኑ ጀመር ።

ለሦስት ዓመታት ያህል እየተዘዋወረ ካስተማረ በኋላ እርሱ ካልተሰቀለና ካልሞተ ፍጹም ሰላም በዓለም ላይ ሊመሠረት አለመቻሉን ለደቀ መዛሙርቱ አስረዳቸው ደቀ መዛሙርቱ ግን እንኳን በሞትና ለአንዲት ጊዜ እንኳ እንዲለያቸው ስለማይፈልጉ መሰቀልና መሞት አይገባህም በሚለው አሳብ ላይ ያተኩሩ ነበር ።

ክርስቶስ ወደዚህ ዓለም መጥቶ እንደሚሰቀልና በመስቀሉም ለዓለም ሁሉ ሰላምን እንደሚያደርግ ቀደም ብሎ ትንቢት ተነግሮ ስለነበር በተነገረው ትንቢት መሠረት ልዩ ልዩ መከራን ተቀብሎ ተሰቅሎ ሞቶ ከተሰቀለም በኋላ በአካለ ነፍስ ወደ ሲኦል ወርዶ ከአዳም ጀምሮ እስከ እርሱ ድረስ ሰላምን አጥተው በመንጸፈ ደይን ወድቀው ይኖሩ ለነበሩ ነፍሳተ ሰብእ ሁሉ ሰላምን ሰጣቸው ነፃነትንም አጐናጸፋቸው በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ደቀ መዛሙርቱ ሰላምን አጥተው ሲጨነቁበት ወደነበረው ቤት ሂዶ ሰላም ለሁላችሁ ይሁን ሲል የሰላምን ቃል አበሠራቸው ።

ከዚያም ፵ ቀን ከደቀ መዛሙርቱ ጋር አብሮ ከቆየ በኋላ ሰላሜን እተውላችኋለሁ ብሎ ነግሯቸው ወደ ሰማይ አርጓል ከማረጉ በፊት ግን የሰው ልጆች ሕጉን ጠብቀው ትእዛዙን አክብረው ቢኖሩ በሰላም እንደሚኖሩ አስተምሯል በሰጠውም ትምህርት ላይ "ሰላሜን እተውላችኋለሁ ሰላሜንም እሰጣችኋለሁ እኔ የምሰጣችሁ ሰላም ዓለም እንደሚሰጠው ያለ አይደለም" በማለት አስረድቷል ዮሐ. ፲፬.፳፯ በዓለም ላይ የሚኖሩ የሰው ልጆች ሰላም ግን በሁለት መንገድ ሊቀርብ ይችላል አንደኛ የልብና የአፍ ሰላም ሲሆን ሁለተኛው ከልብ ጋር ያልተቆራኘ የአፍ ሰላም ነው ከልባቸው ሳይሆን በአፋቸው ብቻ ሰላምን የሚናገሩ ሰዎች ቀድሞም ነበሩ አሁንም አይታጡ የመጨረሻው ዕድላቸው ግን ጥፋት ነው ።

የአፍ ሰላም በማቅረብ ከተጐዱት ሰዎች አንዱ የአስቆሮቱ ሰው ይሁዳ ነው ይሁዳ ከክርስቶስ ደቀ መዛሙርት መካከል አንዱ ነበር የተሰጠው የሥራ ክፍል ገንዘብ እየተቀበለ ማስቀመጥ ነበር እየተቀበለ ከሚያስቀምጠው ገንዘብም ከመቶ አሥር እንዲወስድ ተፈቀዶለት ነበርከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ሴት ፫፻ ዲናር የሚያወጣ ሽቱ አምጥታ በክርስቶስ ራስ ላይ አፈሰሰችው ይሁዳ ከመቶ አሥሩ ስለቀረበት በጣም ተና



www.ethiopianorthodox.org

ደደ ። ሰላምም ፈጽሞ ተለየው ያነን የቀረበትን ገንዘብ ለማግኘት የሚችልበትን ዘዴ ይፈልግ ጀመር ።

በዚያ ወቅት አይሁድ ኢየሱስን ይዘው ለመግደል እየፈለጉ መልኩን ለይተው ለማወቅ ተቸግረው ስለነበር ይሁዳ ፴ ብር ቢሰጡት እንደሚያስይዛቸው ነገራቸው አይሁድም ፴ ብር ወዲያውኑ ስለሰጡት ያንን ተቀብሎ ሰላም ብየ የምስመው ኢየሱስ ነውና ይዛችሁ እድንትሰቅሉት በማለት ከአይሁድ ጋር ተመካክሮ ሄዶ መምህር ሆይ ሰላም ለአንተ ይሁን ብሎ ሳመው ኢየሱስ ግን እውነተኛ ሰላምን ይዞ የመጣ አለመሆኑን አውቆ በመሳም ልታስይዘኝ መጣህን በማለት ሕግ አፍራሽነቱንና ልባዊ ሰላም የሌለው መሆኑን አጋልጦታል ። ይሁዳም የአፍ ሰላም እንጂ የልብ ሰላም ስላልነበረው በመጨረሻ ሰላም ያጣበትን ብር በቤተ መቅደሱ በትኖ ሂዶ ታንቆ ሞቷል ። ማቴ. ፳፮.፳ ።

በአፋቸው ሰላምን እየተነበዩ ከልባቸው ሰላም ስላልሠረጸ ሰዎች ነቢዩ ኤርምያስ ሲናገር "ሰላም ሰላም ይላሉ ሰላምም አልሆነም" ኤር ፰ ፣ ፲፩ ኢሳይያስም "ትእዛዜን ብትሰማ ሰላምህ እንደፈሳሽ በሆነ ጽድቅህም እንደ ባሕር ሞገድ ፣ ከሕግ ለወጡ ግን ሰላም የላቸውም" ብሏል ትን. ኢሳ. ፵፰ ፥ ፲፰ - ፳፪ ።

በዚህ ዓለም ላይ ከሕግ ወጥተው ሰላምን ለማደፍረስ የሞከሩ ብዙ ኃያላን ተነሥተው ነበር ነገር ግን ከሕግ ለወጡ የዘለቄታ ሰላም ሊኖራቸው አይችልምና ከሕግ ወጥተው የሰላምን ኃይል ለማዳከም የሞከሩ ሁሉ አላማቸው ሳይሳካ ከመቅረቱም ሌላ አወዳደቃቸውም የከፋ ሆኖ ቀርቷል ።

ከሕግ ወጥተው ሰላምን ለማናጋት ሲቃጡ ሊወጡት ከማይችሉት የመከራ አዘቅት የወደቁት ብዙ ናቸው ።

አሁንም ቢሆን ልባዊ ሰላም ሳይኖራቸው እንደ አስቆሮቱ ሰው ይሁዳ ከልባቸው ሳይሆን ከአንገታቸው በላይ በአፋቸው ብቻ ሰላምን የሚናገሩ ሰላምንም ለማደፍረስ የሚቃጡ አንዳንድ ኃያላን መኖራቸው የሚያጠራጥር አይደለም ።

ይሁን እንጂ ጠቢቡ ሰሎሞን ጉድጓድን የሚምስ ራሱ ይወድቅበታል ብሎ እንደተናገረው የሰላም ጠንቆችና ሕግ አፍራሾች የሆኑ ሰዎች ሁሉ የመጨረሻው ውጤታቸው ጥፋት ስለሆነ ሰላም የሚሰፍንበትን ሕግ የሚጠበቅበትን መንገድ ተከትለው እንዲራመዱ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ መልእክቷን ከማስተላለፍ አትቆጠብም ።

ቄስ ልሳነ ወርቅ በዛብህ

## የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት

ካገጽ ፲፫ የዞረ

ዘንድ እንዲወገዙና ገበያው እንዲሰናከልበትና እንዲቀዘቅዝ አደረገ ። ኢንፋክት ይህንን እንዴትና ምንስ አደረገ የሚል ቢኖር በኩባንያው ውስጥ ባለው የአክሲዮን ድምፅና የሕፃናትን የአመጋገብና የአስተዳደግ ሁኔታ የሚቆጣጠር ክርስቲያናዊ ድርጅት በመሆኑ የሚል መልስ ያገኛል በአጭሩ በአሥራትና በሙዳዩ ምፅዋት የተገኘው የቤተ ክርስቲያን ገቢ ለበጎና ለዕውነተኛ ነገር ብቻ መዋል እንዳለበት ያስገነዝበናል ።

፪ - አፄ ምኒልክ በኢየሩሳሌም የሚገኘውን ዴር ሱልጣን የተባለውን ገዳማችንን ለመንከባከብና ሐዋርያዊ ተግባሩን እንዲፈጽም ለማድረግ በገዳሙ ስም ከዶር ሊዩኔ በሚባል የፈረንሣይ ባንክ ገንዘብ ሲያስቀምጡለት ያደረጉትን ውል ስንመለከት (በነገራችን ላይ ከውሉ ጽናት የተነሣ ፋሺስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለአምስት ዓመታት በወረረበት ወቅት ገንዘቡን ሊወስደው ፈልጎ አልቻለም) ገንዘቡ ለበጎ ነገር ሥራ ላይ ቢውል እንኳ መነኰሳት ደግሞ ወንጌልን በመዘርጋትና በማስፋፋት ተጠምደው እንዲውሉ መደረጉ ለቤተ ክርስቲያን ትልቅ አስተዋጽኦና መመሪያ መሆኑን እንገነዘባለን ።

፫ - ታላቁ ነቢይ ሙሴ አርባ ቀን ከእግዚአብሔር ጋር በሲና ተራራ ሲነጋገር ከርሞ ሲመለስ ፊቱ ያንጸባርቅ ስለነበር ወገኖቹ ሊያዩት አልቻሉም ። ስለዚህም ሊያነጋግራቸው በፈለገ ጊዜ ፊቱን ይሸፍን እንደነበር ከመጽሐፍ ቅዱስ እንረዳለን ። ከዚህ ልናስተውለው የሚገባ ነገር ቢኖር ከእግዚአብሔር ጋር በመኖሩ ፊቱ እንዲያንጸባርቅና ልዩ ኃይልም መቀበሉን መጐናጸፉንም ነው ።

የክርስትና እምነታችን መሠረት ክርስቶስ አምላካችን ሕይወታችንም ክርስቶስ ነው ። ስምዋ እንደሚያመለክተውም ዓላማዋ እንደሚገልጸውም ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስ አካል ናት ስለዚህም ከክርስቶስ ተለይታ ልትኖር ለጥቂት ደቂቃዎችም ልትቆይ አትችልም። ፳፬ ሰዓት ፫፻፷፭ ቀን ከዓመት ዓመት ከዘመን ዘመን ክርስቶስን ብቻ እንድትመለከት የቤተ ክርስቲያን አባቶች ሊታገሉ ይገባቸዋል ሕይወቷ ነውና ። ሕይወት የሌለው ሁሉ የሞተ ነው የሞተ ደግሞ መበስበሱ የተረጋገጠ ነውና ።

ቤተ ክርስቲያን ክርስቶስን ብቻ የምትመለከትና ከክርስቶስ ጋር ብቻ የምትኖር ከሆነች ለዘለዓለም እንዳበራች እንዳጸባረቀች ትኖራለች ነገር ግን ከክርስቶስ እንድትለይ ለገንዘብ እንድትገዛና በልዩ ልዩ ምክንያት ባዕድ ነገር በጣልቃ እንድታስገባ የሚጥሩ ቢኖሩ ለራሳቸውና ለወገኖቻቸው ጥፋትን ሞትን የሚጋብዙ ብቻ ናቸው ። በተለይም እንዲህ ዓይነቶቹ ከቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችና መምህራን ከሆኑ በራ. ዮሐንስ ፪ ፣ ፭ ላይ "እንግዲህ ከወዴት እንደወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ ፣ የቀደመውንም ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሀለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስድብሃለሁ" የሚለው መለኮታዊ ኃይለ ቃል እንዳይፈጸምባቸው ሊጠነቀቁ ይገባል ።

የቤተ ክርስቲያን ልማትና ኃላፊነት ወንጌልን መስበክ ነው ። የቤተ ክርስቲያን ንግድ ተርፍዋ ምእመናንን በክርስትና ሃይማኖት መኰትኰትና ማስተ

ተከታዩን በገጽ ፳፪ ይመልከቱ



# ዜና ሊቃውንት

## ሊቁ ዓፅሜ (ዐፅመ ጊዮርጊስ ገብረ መሢሕ)

የአሥራ ዘጠነኛውን ምዕት ክፍለ ዘመን ሊቃውንት ዝክረ ነገር በምናጠናበት ወቅት የሊቁ የዓፅመ ጊዮርጊስ ገብረ መሢሕ ታሪክ ከፍ ባለው በታሪክ ገጽታ ላይ ሲያበራና ሲያንፀባርቅ እናገኘዋለን ።

የሊቁ የልደት ዘመን በሁለት ዓይነት አቅጣጫ ስለተጐዳኘ በአንድ በጣም በታወቁ የታሪክ ተመራማሪ በ፲፰፻፲፫ ዓ.ም. ተወልደው እንደ ነበረ ሲጠቁም ከቤተ ዘመዶቻቸው በተገኘው የታሪክ ይዘትና ቅንብር ደግሞ የልደታቸው ዜና ሳይሆን በተወለዱ በ፹፪ ዓመት ዕድሜያቸው በ፲፱፻፯ ዓ.ም ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩ መሆናቸው ተገልጿል ።

እንዲሁም ለዚህ ተጨማሪ የሆነው አጠናካሪ የታሪክ ማስረጃ በተወለዱ በ፴ ዘመናቸው በቁርባንና በሕግ ማስትማግባታቸውን ስለሚያረጋግጥና ሰፋ ያለውን የትምህርት መዋቅራቸውን አጠናቅረውና ፈር አስይዘው ከአከለ ጉዛይ ወደትውልድ አገራቸው የተመለሱት በ፲፰፻፰፰ ዓ.ም የሚያስኝ መሆኑን ብዙዎች የታሪክ ሰዎችም ተስማምተውበታል ።

በመሆኑም ከ፲፰፻፳፭ ላይ ፴ ሲቀነስ በ፲፰፻፹፭ ዓ.ም መወለዳቸው በ፲፱፻፯ ዓም በ፹፪ ዓመታቸው መሞታቸው ተረጋግጧል ማለት ነው ።

የሊቁ የትውልድ አገር በሸዋ በቴጉለትና ቡልጋ አውራጃ አንኮበር ወረዳ ልዩ ስሙ ሐር አምባ እየተባለ በመጠራት ከታወቀው አካባቢ ነው ።

ዓፅሜ ካንዱ ወደሌላው ትምህርት ቤት በመዘዋወር በመጀመሪያ ደረጃ የንባብ ትምህርታቸውን ከተከታተሉና ዳዊት ከደገሙ በኋላ ዜማ ቅኔ ተምረዋል ፣ ቀጥሎም የሐዲሳትን ፣ የመጻሕፍቱ ሊቃውንትንና የመጻሕፍተ ብሉያትን ትርጓሜ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት በሚገባ አደላድለው ዐውቀዋል ።

ሊቁ በብሔራዊ ትምህርት ብቻ ምርምራቸውንና የዕውቀት ይዞታቸውን ሊወስኑ ወይም ሊገቱ ስለአልፈቀዱ ወደ አፋር በረሃ ተጉዘው "ፍሬ" እየተባለች ከምትጠራ ቦታ የዓረብኛ ቋንቋ ተምረዋል ።

ከዚህም በኋላ ወደ ሰሜን ኢትዮጵያ ሔደው አባ ያዕቆብ ወይም ዲ.ጃኮቢስ ከሚባሉ የላዛሪስት ሚስዮን ምሁር የላቲንና የፈረንሣይ ቋንቋ እጅግ ደስ በሚያሰኝ ሁኔታ አጥንተዋል ።

ሊቁ ዓፅሜ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለትምህርትና ለመንፈሳዊ አገልግሎት የምታውላቸው የግዕዝ መጻሕፍት በመሠረቱ የተመለሱባቸውን ወይም የተተረጐሙባቸውን መጻሕፍት ለማመሳከርና ለማስተያየት ብርቱ ፍላጐት ስለነበራቸው የዕብራይስጥን ቋንቋ በተጣራ ሁኔታ ተምረዋል ።

ቀጥሎም ወደሸዋ ተመልሰው አባ ማስያስ ከተባሉ ኢጣልያዊ መነኩሴ ዘንድ የኢጣልያ ቋንቋ ተከታትለው ዐውቀዋል ።

እንግዲህ ሊቁ በጠቅላላው አጣርተው የሚያውቋቸው ቋንቋዎች ከግዕዝ ጋር ስድስት መሆናቸው ነውና ከብሔራዊው የትምህርት አቋማቸው ጋር እነዚህ ሲደመሩ በደረጃ ከከፍተኛው የኢትዮጵያ ሊቃውንት የታሪክ መድረክ ላይ ብናቆማቸው ያለሞያቸው ስም መስጠትና ማጋነን አይሆንብንም ።

ዓፅሜ "ተምሮ አለማስተማር እንዲቷን መክሊት ቆፍሮ እንደቀበረው ሰነፍ አገልጋይ ነው " በሚለው የዘወትር መፈክር እየተመሩ እየተዘዋወሩ በሚማሩበትም ጊዜ ሆነ በትውልድ አገራቸው ሳሉ ከማስተማርና የትምህርት መክሊታቸውን ከማራባት የተገቱበት ጊዜ ላለመኖሩ ደቀመዛሙርቶቻቸው የሆኑት ሊቃውንት ማስረጃዎች ናቸው ።

በሀገር ፍቅርና በፖለቲካዊ ተግባር

ሊቁ ባጠናቀሯቸው የትምህርት ዓይነቶችና ስሜታቸው እየተረዱ ለኢትዮጵያዊት አገራቸው በሀገር ፍቅር ረገድና በፖለቲካዊ ይዘት ያበረከቱት አስተዋፅኦ ስማቸውን በታሪክ ሕያው አድርጎታል ።

ለማስረጃም ያህል በ፲፰፻፷፰ ዓ.ም የዓረብ ነጋዴ መስለውና በሐረርጌ ለሦስት ወራት ያህል ቆይተው በወሰዱት ጥናት ስለሕዝቡ ኑሮ ፣ በጊዜው ስለነበረው የጦር ብዛትና ሚዛን የተሟላ ሪፖርት ለዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ በማቅረባቸው ዓፄ ምኒልክ በ፲፰፻፸፱ ዓ.ም ሐረርጌን ለመክፈትና በቀላሉ ድል ለማድረግ ችለዋል ።

ከዚህም ጋር ሊቁ የሥነ ጽሑፍ ባለሙያ መሆናቸው በታሪክ ታውቋል ። ሆኖም ስለሥጋዊ ፣ ስለመንፈሳዊና ፣ ስለፖለቲካ እንዲሁም ስለሀገር ፍቅር የጻፏቸው ሥነ ጽሑፎች ተሟልተው ተዘጋጅተው በሁለት ሣጥኖች ሞልተው እንደታሸጉ በጣላት ወረራ የአንኮበር ከተማ በቦምብ ሲደበደብ ተቃጥለው በመቅረታቸው የሊቁ የረጅም ጊዜ ድካም ያለፍሬ ቀርቷል ።

ከላይ እንዳመለከትነው ሁሉ ሊቁ የፖለቲካ ሰው ነበሩና ጀርመን ቤልጅግ ፈረንሣይና እንግሊዝ አፍሪካን በቅኝግዛት ለመከፋፈል ያደርጉት ከነበረው ወቅታዊ ጥናት ባሻገር ኢጣልያም ኢትዮጵያን ለመውረር ታደርግ የነበረውን የግፍዕና የዕብሪት ዝግጅት ተገንዝበውት ስለነበረ ይኸንኑ በማስመልከት ለዳግማዊ ዓፄ ምኒልክ ያቀረቡት የመቀስቀሻ ሪፖርት ለታሪካቸው ተጨማሪ ኃይል ሊሰጠው ችሏል ።

ይሁን እንጂ የሊቁን አገር ወዳድነትና የፖለቲካ ይዘት በትክክል ያልተገነዘቡት አንዳንድ እንብላ ባዮች በሸረቡት ሤራ ባልተጨበጠ ማስረጃና ባልተጣራ ሁኔታ ለአንድ ዓመት ያህል ታስረው በግዞት እንዲቆዩና አንድ መቶ ብር መቀጮ እንዲከፍሉ ተደረገ ።

በዚያን ጊዜ ከነበሩት ኢትዮጵያውያን መካከል ለሥልጣኔና ለፍሬ ከበቁት ከጥቂቶቹ አንዱ የነበሩት ዓፅሜ የደረሰባቸው መንገላታትና እሥራት ባልተጣራ ሁኔታ መሆኑ ተገምግሞ በዓፄ ምኒ

ተከታዩ ወደ ፱ኛው ገጽ ዞሯል



www.ethiopianorthodox.org

## መስከረም

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ የ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የዘመን መለወጫን በዓል ምክንያት በማድረግ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ቡራኬና መንፈሳዊ መልእክት በሬዲዮና በቴሌቪዥን አስተላልፈዋል ።

ፓትርያርኩ መስከረም ፲፯ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በዓለ መስቀልን ከብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳትና በብዙ ሺ ከሚቆጠሩ ምእመናን ጋር አክብረዋል ።

ቅዱስነታቸው በበዓሉ ለተገኙት ምእመናን ነገረ መስቀሉን አመልክተው ቃለምእዳን አሰምተዋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ የቅዱስ ጳውሎስ ከፍተኛ ት/ቤት ተብሎ በቅዱስ ሲኖዶስ የተሰየመውን ሕንፃ መስከረም ፳፩ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ጐብኝተዋል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ መስከረም ፳፯ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ረቡዕ ከቀኑ በስድስት ሰዓት ወደ አውሮጳ ሔደዋል።

ቅዱስነታቸው ጉብኝት እንዲያደርጉ ጥሪ የተደረገላቸው ከኦስትሪያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከምዕራብ ጀርመን ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን ነው እንዲሁም ከሮማው ፓፓ ጋር በቫቲካን ተገናኝተው አሳብ ለአሳብ ተለዋውጠዋል ።

## ጥቅምት

የ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ቅዱስ ሲኖዶስ ከጥቅምት ፲፱ - ፳፩ ቀናት በቅዱስነታቸው ሰብሳቢነት ተሰብስቦ በአራት ነጥቦች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፎአል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከጥቅምት ፳፰ -ኅዳር ፲፯ ቀን የጐንደርንና የጐጃምን ታሪካውያን ቦታዎችና አብያተ ክርስቲያናት ጐብኝተዋል ።

## ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ማኅደር

(ከንቅዓ ጥበብ ወንድም)

## ኅዳር

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ኅዳር ፳፱ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በእስክንድርያ የአርመን ሊቀ ጳጳስ ዘቤን ኪንቻማይን በመንበረ ፓትርያርኩ ልዩ ጽ/ቤት ተቀብለው አነጋግረዋል ።

## ታኅሣሥ

ቅዱስነታቸው ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በቁልቢ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው በመልአኩ ስም ለተሰበሰበው ሕዝብ ቡራኬና መንፈሳዊ መልእክት ከማሰማታቸውም በላይ በድሬደዋ ከተማ በሚገኘው በቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ተገኝተው ለካህናቱ መመሪያ ሰጥተዋል ።

በ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ቅዱስ ፓትርያርኩ ታኅሣሥ ፳፩ ቀን በሰላሌ አውራጃ በግራር ጃርሶ ወረዳ ፍቼ ከተማ አካባቢ የምትገኘውን ጥንታዊቷን አሩተ ማርያም ቤተ ክርስቲያን ጐብኝተዋል መመሪያም ሰጥተዋል ።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን በዓለ ልደት ምክንያት በማድረግ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ለመላዋ የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን በሬዲዮና በቴሌቪዥን ቃለ ምእዳን አስተላልፈዋል ።

## ጥር

ከጥር ፮ - ፰ ድረስ ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን በልማት ኮሚሽን አማካይነት የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ርዳታ ሰጭ ድርጅት በናዝሬት ከተማ በአዳማ ራስ ሆቴል ተሰብስቦ ስለእርዳታው አሰጣጥ ተወያይቶ ውሳኔ አስተላልፎአል ።

ጥር ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ በዓለ ጥምቀት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት በተገኙበት በአዲስ አበባ ከተማ ከፍ ባለ ድምቀትና መንፈሳዊ ሥነ ሥርዓት ተከብሮአል ።

## የካቲት

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ በተገኙበት የካቲት ፲፱ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. ለኢትዮጵያ ሰማዕታት በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ከጧቱ ፬ ሰዓት ጀምሮ ጸሎተ ፍትሐት ተደርጓል ።

## ሚያዝያ

፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የተከበረውን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በዓል ምክንያት በማድረግ ብፁዕ ወቅዱስነታቸው ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝበ ክርስቲያን ሚያዝያ ፱ ቀን ቡራኬና ምዕዳን በሬዲዮና በቴሌቪዥን አስተላልፈዋል ።

## ግንቦት

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ከግንቦት ፱ - ፮ ቀን በሶቭዬት ኅብረት በመስኮቭ ከተማ በተደረገው ዓለም አቀፍ የሰላም ጉባኤ የቤተ ክርስቲያንን የሰላም ልዑካን በመምራት ተገኝተዋል ።

በጉባኤውም መንፈሳዊ መልእክት አሰምተዋል ያሰሙትም መልእክት በሬዲዮ መተላለፉ ታውቋል ።

ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ሊቃነ ጳጳሳት በተገኙበት በጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅ በሊቀ ማዕምራን አበባው ይግዛው ሊቀመንበርነት የሚመራ ጉባኤ ከግንቦት ፴-ሰኔ ፯ ቀን በጠቅላይ ቤተ ክህነት ስብከተ ወንጌል አዳራሽ አጠቃላይ የሰበካ ጉባኤ ሰሚናር ተካሒዷል ።

ጉባኤውም ከተወያየ በኋላ ባለ ፲፰ ዓበይት ነጥቦች በውሳኔ አስተላልፎአል ።

በፓትርያርኩ ሊቀ መንበርነት የሚመራው ቅዱስ ሲኖዶስ ከግንቦት ፴ - ሰኔ ፲፭ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. መደበኛ ስብሰባውን አካሒዷል ቅዱስ ሲኖዶስ በሰፊው ከተወያየ በኋላም ውሳኔ አስተላልፎአል ።



# ልማት በቤተ ክርስቲያን

## የአዋሽ ፯ ኪሎ ሜትር ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም

ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ራስዋን በራስዋ ለመምራት ባላት እቅድ ምእመናንዋን በየአጥቢያው አብያተ ክርስቲያናት በሰበካ ማኅበረ ምእመናን እያደራጀች ናት ።

የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ሕይወት የሆኑ ምእመናንም በወጣው ቃለ ዓዋዲ መሠረት መብታቸውን ለማስጠበቅ መንፈሳዊ ግዴታቸውን እያሟሉ ይገኛሉ

ለምሳሌ በቃለዓዋዲው ደንምብ አንቀጽ ፵፫ ንዑስ አንቀጽ ፱ መሠረት በአንዲት የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ሰበካ ክልል ውስጥ የሚኖሩ ምእመናን በገንዘብ አስተዋጽኦ ፣ በአስተዳደር ፣ በልማትና በማኅበራዊ ኑሮ አገልግሎት ፣ በጠቅላላው በሀብት ፣ በዕውቀትና በጉልበት ቅ/ቤተ ክርስቲያንን መርዳት እንዳለባቸው ያስረዳል ።

በዚሁ መሠረት በአዋሽ ፯ ኪሎ ከተማ ውስጥ በምትገኘው ደብረ ሰላም ቅማርያም ቤተ ክርስቲያን ያሉ ምእመናን ደንቡ በሚያዘው መሠረት በአባልነት ተመዝግበው የሚፈለግባቸውን ወርሐዊ (ዓመታዊ) አስተዋጽኦ ከመክፈላቸውም ሌላ ቃለዓዋዲው በዓንቀጽ ፲፰ ንዑስ ዓንቀጽ ፩ እና ፱ በአንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ ፩ እና ፱ መሠረት በሰበካ ጉባኤው እቅድና በራሳቸው ፍላጐት የልማት ሥራዎችን እየሠሩና በይበልጥ ለመሥራትም እየተዘጋጁ መሆናቸውን የደብርዋ አስተዳዳሪ መምሬ ማሞ ጉርሙና የሰበካ ጉባኤው ጸሐፊ መምሬ መኰንን ወ/ማርያም አስረድተዋል ።

ጥያቄ፡- በአጥቢያው ክልል ውስጥ የሚገኙ ምእመናን ስንት ይሆናሉ ?

መልስ፡- በአጥቢያው ክልል የሚገኙ ምእመናን እጅግ በጣም ጥቂቶች ናቸው ይሁን እንጂ እኒሁ ጥቂት ምእመናን የሚያኮሩ መንፈሳዊ አስተዋጽኦ እያደረጉ በመሆናቸው እንኮራባቸዋለን ፤

ጥያቄ ፡- ምእመናኑ ጥቂቶች መሆናቸውን አረጋግጣችሁ በመንፈሳዊ አስተዋጽኦዋቸው በመኩራታችሁ እንደነቃለን ምን ዓይነት ሥራዎችን ቢሠሩነው?

መልስ፡- ምእመናኑ ጥቂት በመሆናቸው የቤተ ክርስቲያንዋን አገልግሎት ሊያቃኑት አልቻሉም ፣ በመሆኑም በሰበካ ጉባኤ ዓመታዊ (ወርሐዊ) አስተዋጽኦ ፲፱ ብር መክፈል ሲገባ በዓመት እስከ ፰ ብር የሚከፍሉ አሉን ለምሳሌ ያህል እነወ/ሮ ዘለቃሽ ገብሬና እንደሳቸው የሚከፍሉትን መጥቀሱ ይበቃል ። ከዚህ ሌላ ቀጥለን በዝርዝር የምናቀርባቸው በራሳቸው ፍላጐት ፩ኛ/ ወ/ሮ አበበች ባቡ በቅርብ ጊዜ በሞት የተለዩንና ዛሬ ልጃቸውን የተኩልን በቤተ ክርስቲያን ንዋየ ቅድሳት ቢጐድል ፣ የካህናት አበል ቢያጥር ለማሟላት ቃል



ወ/ሮ ሙላት እንግዳ ወርቅ

የገቡና እያሟሉም የኖሩ ፣

፱ኛ/ወ/ሮ ሙላት እንግዳ ወርቅ ለቤተ ክርስቲያኑ ከ፴ሺህ ብር (አራት ሺህ) በላይ ከፍለው ድምፅ ማጉያ የገዙና ለቤተ ክርስቲያንዣ የውሃ ቧንቧ የረዱ ለወደፊትም በዚሁ መሠረት ያለምንም ጐትጓች የሚረዱ ፣

፫ኛ/ ወ/ሮ ማዳብያዊ አስማኮፓሎስ ግሪካዊት የቤተ ክርስቲያንዋ መብራት የቆጠረውን ሂሣብ በየወሩ የሚከፍሉ ፣

፬ኛ/ ወ/ሮ ወርቁ ተሰማ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ደካሞችን በመርዳ



ወ/ሮ ወርቁ ተሰማ

ትና የተጣሉትን በማስታረቅ ፣ በተለይም ስለ አሥራት አስተዋጽኦ ብዙ ክርስቲያኖችን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሳብ የገንዘብ አስተዋጽኦ በማስደረግ ፣ ለልማት ሥራ በመጀመሪያ ደረጃ ሰዎችን ማሳመንና ወደ እግዚአብሔር ማቅረብ ጠቃሚ ይሆናል ብለው ጥሩ ውጤት ያስገኙ ናቸው ።

፩ኛ/ወ/ሮ ጽጌ አጽብሐና ወ/ሮ ዘውዴ ወንድም አገኘሁ የቤተ ክርስቲያኗን የውስጥና የውጭ ግድግዳ ቀለም ያስቀቡና የወደፊትም አስተዋጽኦዋቸው ይህ የሆነ

፮ኛ/ አቶ ብርሃኑ ተሊላና አቶ ሽበቶ ወ ሚካኤል ቀለም በመቀባት በጉልበትና በገንዘብ የሚረዱ ፣

፯ኛ/ ወ/ሮ ወርቅነሽ ገሠሠ ለቤተ ክርስቲያኑ የደወል ቤት ቆርቆሮ የገዙና ለወደፊትም በሕይወት እስካሉ ድረስ ለቤተ ክርስቲያንዋ አገልግሎት የሚውል ገንዘብ በራሳቸው ፈቃድ የሚከፍሉ መሆናቸውን ቃል ገብተው አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ፣

፰ኛ/ አቶ ተሊላ ጫካ በየዓመቱ አስተርእዮና ጥምቀትን ለሚያከብሩ ካህናትና ምእመናን ለማስተናገድ ሕዝብን በማስተባበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ።

፱ኛ/የአባት ጦር አባሎች የደወል ቤትና ዕቃ ቤት በግምብ አሠርተዋል ለወደፊትም ቤተ ክርስቲያንዋ በነፋስ ኃይል ጉዳት ቢደርስባት በጥገና በኩል



www.ethiopianorthodox.org

ያለምንም ክፍያ ይሠራሉ በአጠቃላይ የገንዘብ አስተዋጽኦ አስቀድሞ በምእመናኑ ፍላጎት በክፍፍል የተያዙ በመሆኑ እንዱስትሪ አቋቁመናል ለማለት አስደፍሮናል ።

ጥያቄ ፦ የገንዘብ ፣ የዕውቀትና የጉልበት አስተዋጽኦ የሚያደርጉ እነዚህ ብቻ ናቸው ማለት ነው ?

መልስ፦በሰበካ ጉባኤ ያልተመዘገበና አስተዋጽኦውን የማይከፍል የለም እነዚህ ግን በራሳቸው ፍላጎት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉና የሚያደርጉ በመሆናቸው ጠቀስናቸው እንጂ እነመቶ አለቃ ታምሩ ገዳ ፣ ሻምበል መንግሥቱ ፈቅይበሉና ፲ አለቃ አምዛ በሽርን የመሳሰሉ ተባባሪዎች አሉን ።

ጥያቄ ፦ ምእመናኑ ያሳዩት ትብብር ለሌሎች በምሳሌነት ሊጠቀስ የሚገባው ነው ነገር ግን ከዚህ የተለየ የዕለት ገቢ የሚያስገኝ ልማት አቋቁማችኋል?

መልስ ፦ እነዚህ ምእመናን በዕለት ፣ በወር ወይም በዓመት የተወሰነ ክፍያ ለመስጠት አልወሰኑም ካላቸው ገቢ ለቤተ ክርስቲያንዋ ከአስር አንድ እያዋጡ በሳጥናቸው ያስቀምጣሉ ይህ ዓይነቱ አስተዋጽኦ የተለየ ልማት ነው ብለን እምነንበታል ፣ ሆኖም ከዚህ በፊት ከልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ፲ ሺህ ብር አግኝተን ለቤተ ክርስቲያንዋ መብራት እንዳገባን ሁሉ አሁንም ምእመናኑ ባዋጡት ገንዘብ ላይ እርዳታ አግኝተን በቅርብ ጊዜ የዳቦ ቤት ለመክፈት አቅደናል ።

በልማቱ ረገድ በማጠቃለል የምናቀርበው በሰበካ ጉባኤ የተመዘገቡ ምእመናን በየወሩ ሳያቋርጡ መክፈላቸው ፣ በየዕለቱ በየሳምንቱና በየወሩ የሚያዋጡት ሙዳየ ምፅዋት ፣ እየተጠናከረመሔዱ ፣ በሌላ በኩል በሰበካ ጉባኤ ደንብ መሠረት ፩ኛ/ ፫ ብር ፪ኛ/ ፮ ብር ፫ኛ/ ፲፪ ብር ፬ኛ/ ፳፬ ብር ከነዚህ አንዱን መክፈል ሲገባቸው በዓመት ፳ ብር መክፈል ምእመናኑን ወደ ልማት መለወጥ በመሆኑ የሚያስደስትና መንፈሳዊ ቅናትን የሚያሳድር ነው ብለዋል ።

ከዚህ በኋላ ለቤተ ክርስቲያንዋ ዕድገት በመንፈሳዊ ፍላጎት ገንዘባቸውን፣ ዕውቀታቸውንና ጉልበታቸውን ከሚያዋጡት መካከል ወ/ሮ ሙላት እንግዳንና ወ/ሮ ወርቄ ተሰማን አነጋግረናል ።

ጥያቄ፦ወ/ሮ ሙለት ለቤተ ክርስቲያን እድገት እንደሚጥሩ ተረድተናል ያደረጉት አስተዋጽኦ ምንድን ነው ?

መልስ ፦ ይህን አደረግሁ ማለቱ ደስ አይልም እንጂ ከዚህ በፊት ካደረግሁት ጐልቶ የሚታየው ድምፅ ማጉያ፣ የውሃ ቧንቧ ፣ እና የሚፈለገውን ሁሉ አድርጌ አለሁ ።

ጥያቄ ፦ ለወደፊትስ ምን ለመሥራት አቅደዋል ?

መልስ ፦ እኔ ለሥጋዊ ሕይወቴ ብዙ ሥራዎችን ሠርቼአለሁ ግን በቂ ሆኖ አላገኘሁትም አሁን ግን ለመንፈሳዊ ሕይወቴ ክቡና ቤቴ የሚገኘውን ገቢ ከ፲ አንድ በማውጣት በማርያም ስም አስቀምጣለሁ ለቤተ ክርስቲያንዋ የሚያስፈልግ ነገር ሲገኝ በዚህ ዓይነት ከተደራጁ ወንድሞችና እህቶች ጋር አዳምረን እንሠራለን በቂ ሆኖ ባይገኝ ግን የሚፈለገውን አዋጥተን እናሠራለን ።

ጥያቄ፦ ወ/ሮ ወርቄ ተሰማ ለቤተ ክርስቲያናችሁ የምታደርጉት አስተዋጽኦ የሚያስደስት ነው፡እስከ መጨረሻው ያለዎ እቅድ ምን እንደሆነ ቢገልጹልን ?

መልስ፦ እንደሚታወቀው ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያናችን ባልዋት የምእመናን ብዛት አኳያ ሌሎችን መርዳት ስትችል ተረጂ ሆና የምናያት ምእመናንዋን በአስራት አስተዋጽኦ የሚያለማምዳቸው ባለመኖሩ ነው እኔ በዚህ ረገድ ጥሩ ገቢ እያላቸው የማይሰጡ ፣ ተፋቅረው መኖር ሲችሉ በሆነው ባልሆነው የሚጣሉ በዚች ጠባብ ከተማ ስላሉ ለመንፈሳዊ ሕይወታቸው ካላቸው ከ፲ አንድ እንዲሰጡ በየዕለቱና በየሳምንቱ ለእግዚአብሔር የሚሰጡትን ገንዘብ አስቀምጠው ሙዳየ ምፅዋት እንዲሰጡ ሳደርግ ፣ በቤተ ክርስቲያን በማርያም ስም ማኅበር እንዲገቡ እየተጣጣርኩ ነኝ ጥሩ ውጤትም አስገኝቻለሁ ፣ በሌላም በኩል የተጣሉትን በማስታረቅ ረገድ እያስታረቅሁ ወደቤተ ክርስቲያን እየሳብኩ በመሆኔ ለነሱ ብቻ ሳይሆን እኔም ደስታ ይሰማኛል ከዚህም ጋር ችግረኞችን በመርዳት ለአምላኬዬ አገለግላለሁ ይህ አሠራር በአጭሩ እንዳይቋጭ እስከመጨረሻው ለመሥራት ቃል ገብቻለሁ ብለዋል ።

ከነመምሬ ማሞ ጉርሙ መልስና ከምእመናኑም አንዳንዶቹን ጠይቀን እንደተረዳነው ከምእመናኑ ለጥገና ሥራ የተለዩ ሰዎች ተመድበው መቀመጣቸው ፣ የአሥራት አስተዋጽኦን ለማስለመድና ለማጠናከር የሚደረገው ጥረት፡ በሰበካ ጉባኤ ቢያንስ ፮ ቢበዛ ፳፬ መክፈል ሲገባ በየዓመቱ ፳ ብር መክፈላቸው ፣ በሌላ በኩል ቤተ ክርስቲያንዋ የተገለገለችበትን የመብራትና የውሃ አገልግሎት ሂሣብ በየወሩ የሚከፍሉ ሰዎች መኖራቸው የሚያስመሰግን ነው ለሌሎችም በምሳሌነት የሚቀርብ ነው ይህ ዓይነቱ የልማት አስተዋጽኦ በሌሎችም ቦታዎች ቢለመድ መልካም ነው ።

በለጠ አበበ

## የቤተ ክርስቲያን ኃላፊነት

ከገጽ ፲፰ የዞረ

ማርያም ነው ።

ወንጌልን ተርበናል መምህራን የትናችሁ ወንጌልን ተጠምተናል መምህራን የትናችሁ ? ኧ ......ረ የ....ት ና...ች ......ሁ ።

ማሳሰቢያ

በመጨረሻ የሚገኘው ‘‘ኧረ የትናችሁ’’ የሚለው ሐረግ ሆሄያት ፈንጠር ሐፈንጠር ብለው የተቀመጡበት ምክንያት በገጠሪቱ ኢትዮጵያ አንድ ሰው ዘመድ አዝማዱን ለዕርዳታ በሚጠራበት ጊዜ ያለውን የድምፅ ሁኔታ ያመለክታል ምክንያቱም ጠሪውና ተጠሪው ተራርቀው ይገኛሉና ።

ከኢኩሜን መጽሔት ቁጥር ፯
ታኅሣሥ ፲፱፻፸፩
ገጽ ፵፪ - ፵፫
እንግዳ ወርቅ ጥሩነህ



# የቤተሰብ ዓምድ

አዘጋጅ ንብረት አበበ

የቤተሰብ ሥራ በቤት ውስጥ ለሚገኙት ብቻ የተወሰነ አይደለም ። የክርስቲያን ቤተሰብ መልካም የሆኑ እውነተኛ የሕይወት ደንቦች የሚገለጹበት የበጐ ነገሮች ሁሉ ምሳሌ መሆን አለበት የዚህ ዓይነቱ ምሳሌነት በዓለም ውስጥ ጠቃሚ ኃይል መሆኑ አያጠራጥርም ። ከማንኛውም ስብከት ይልቅ የሰውን ልብና ሕይወት በበለጠ ሊለውጥ የሚችል የመልካም ቤተሰብ ምሳሌነት ነው ከእንዲህ ዓይነት ቤተሰብ የሚገኙ ሁሉ በሕይወታቸው የሚኖረው ሥርዓትና ደንብ በውጤቱ አቻ አይገኝለትም ።ከቤተሰብ ቤተሰብ የሚተላለፈው የተከበረ የሕይወት ሥርዓት ወደሌሎች ሲዳረስ የሚያስገኘው ውጤት የተትረፈረፈ ነው ስለዚህም መልካም ቤተሰብ ለብዙ ሰዎች በረከት ሊሆን ይችላል ማለት ነው ። ርኅራኄአችን ከራሳችንና ከቤተሰባችን አልፎ ለሌሎች መዳረስ አለበት ። ይህም በኀዘንና በግድ ሳይሆን በደስታና በፍቅር ሊሆን ይገባል ። ብዙ ከተሰጣቸው ሰዎች ብዙ ይፈለግባቸዋልና ነው ። ፈቃደኝነት ካለ ቤትን ለሌሎች መባረኪያ ለማድረግ የሚፈልጉ ካሉ መልካም ዕድል ሞልቷል ። ቤታችን ፈተና ለሚደርስባቸው ሁሉ መከላከያ ምሽግ ሊሆን ይችላል ሀላፊነታችን ሳንፈቅድ ከራሳችን ለሚገኙ ብቻ ሳይሆን ከሌሎች ተገኝተው ፈተና ላጠቃቸው ሁሉ እጃችን ለበጐ ነገር ሁሉ መዘርጋት አለበት በጐ ነገር ምንድነው ቢሉ ያዕቆብ በመልዕክቱ እንደጻፈው ወላጆች የሌላቸውን ልጆችና ባልቴቶችን በመከራቸው መጠየቅ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነትን መጠበቅ ነው ሲል እንደገለፀው ማለት ነው ።

ይህንኑ በመረዳት ይመስላል የራሳቸው ያልሆኑ (ያልወለዱአቸውን) እንደራሳቸው ልጆች በማየት ከአሥራ ሁለት ልጆች በላይ በማሳደግና በማስተማር ታላቅ አስተዋጽአቸውን በፍቃዳቸው ያበረከቱት የዚህ ቤተሰብ ዓምድ ቀደም ብሎ እንደሚታወቀው ሁሉ መልካም አርአያነት ካላቸው ቤተሰቦች መካከል ጥቂቶቹን ስናስተዋውቃችሁ መቆየታችን ይታወሳል በዚህ ጽሑፋችን ደግሞ ከሚበልጥም የሚበልጥ አለ እንዲሉ ከላይ እንደተገለጸው የወለዱአቸውን አይደለም ማንም አላስገደዳቸውም ፣ በራሳቸው ፍላጎትና ርህራሄ ብቻ ከሚረዱአቸው ሌላ ከ፲፪ ልጆች በላይ የሚያስፈልጋቸውን ጥበቃና እያያዝ በማድረግና ለአሁኑ እንደሚያስፈልጋቸው በመረዳት ለወደፊቱም እራሳቸውን እየረዱ ለመኖር በሚያዘጋጃቸው ሁኔታ በማስተማር በሃይማኖትና በምግባር አንጸውና ኰትኩተው በማሳደግ ድርሻቸውን አበርክተዋል ስለዚህ በመልካም ቤተሰብ መሪነታቸው እኚሁ ሴት ቢጠቀሱ አርአያነታቸው ጠቃሚ ሊሆን እንደሚችል ስለተረዳን ወ/ሮ ደስታ ገለልቻን ከነቤተሰቦቻቸው እናስተዋውቃችኋለን ።

አስቀድመን የእርሳቸውን ታሪክ ከረጅሙ ባጭሩ እንመለከታለን ካሉበት ሄደን በማነጋገር ያገኘነው ወ/ሮ ደስታ ይላሉ በመናገሻ ወረዳ ልዩ ስሙ በርፈታ በሚባለው ስፍራ በ፲፱፻፳፬ ዓ.ም ከአባታቸው ከአቶ ገለልቻና ከእናታቸው ከእመት ፈለቀች ሀይሌ ተወለዱ ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ የአማርኛ ትምህርታቸውን በመናገሻ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን እንዳጠናቀቁ ወዲያው ደግሞ ውዳሴ ማርያምን ተምረው ፈጽመዋል ከዘመናዊውም ትምህርት እስከ ስድስተኛ ክፍል እንደደረሱ በሀገሩ ባህል መሠረት ለአቅመ ሄዋን ደርሰዋል ብለው ቤተሰቦቻቸው በገመቱበት ወቅት ዳሩአቸው ። ወ/ሮ ደስታ ይህ ጋብቻ በዚያን ጊዜ የተፈፀመ በሀገር ባህል ወግ እንጂ እንደ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ባይሆንም እኔ ግን በሥጋወደሙ የመወሰን ሀሳብ እያደረብኝ ሄደ ይኸም እኔ በፈለኩበት ወቅት ሊፈፀም አልቻለም ። ከባለቤቴ ከአቶ አሊፎም አባይ ጋር ፳፭ ዓመት ያህል ስንኖር የወለድነው ልጅ አንድ ነው እሱም አሁን በውጪ አገር ከፍተኛ ትምህርቱን በመከታተል ላይ ይገኛል ባለቤ



ወ/ሮ ደስታ ገለልቻ ከሚረዱአቸው ልጆች ጋር



www.ethiopianorthodox.org

ቴን ንስሐ ገብተን ሥጋወደሙ ተቀብ
ለን እንድንኖር ስጠይቀው እሱ ፈቃደ
ኛ አልነበረም እኔ ግን ባለመሰልቸት
ጧትና ማታ ስጨቀጭቀው ገና ነኝ
በማለት የመለሰልኝን መልስ እስካሁን
አልረሳውም ። በዚህ ሁኔታ ላይ እንዳ
ለን በሃያ አምስት የጋብቻ ዘመናችን
እሱ በድንገተኛ አደጋ እንደወጣ ቀረ እ
ኔም ታዲያ ያ ሀሳብ በልቤ ነበርና ሰው
በዚህ ዓለም የሚኖረው አንድ ጊዜ ብቻ
ነው እንግዲህ ወደ ዓለም አልመለስም
በማለት ከሱ ጋር በዚሁ ሁኔታ ከተ
ለያየን በኋላ በትዳር በኩል ብቸኛነትን
በመምረጥ ችግረኞችን እየረዳሁ ከችግ
ረኞች ጋር ብኖር የምደሰትበትና ከሁሉ
ም የሚሻል መሆኑን ተረዳሁ በዚሁም
እዘልቅበት እንደሆን እራሴን ቀስ በቀ
ስ በመመርመር ምርጫዬን ይኸን አደ
ረኩ ይላሉ ። አሁን የሚተዳደሩበትና የ
ሚረዱአቸውን ሕጻናት የሚያስተዳድ
ሩት በምን እንደሆነ ለጠየቅናቸው
ሲመልሱ ። የቤንዚን ማደያ ባለንብረት
መሆናቸውን ገልፀውልናል በዚህም
ለእርሻቸውና ለሚረዱአቸው በቂ መሆ
ኑን ገልጸውልናል ።

ወ/ሮ ደስታን በዚሁ ሁኔታ በበለ
ጠ የሚደሰቱበት በየትኛው እንደሆነ ለ
ጠየቅናቸው ሲመልሱ ሕጻናትን ማሳደ
ግና ማስተማር ደስ ይለኛል ብለዋል
ከእነዚህም መካከል ወላጆች የሞቱባቸ
ውና ቢኖሩአቸውም ሊያሳድጉአቸው
ያልቻሉትን ፣ በበሽታ ምክንያት በመሰ
ቃየት ረዳት ያጡትንና መጠጊያ የሌላ
ቸውን ሲሆን ሊረዱ ይገባቸዋል ብዬ
ሙሉ በሙሉ በመተማመን ነው ሲሉ
ገልጸውልናል ። ከረዳኋቸው መካከል
ዛሬም በአጠገቤ ቢገኙም በትዳርና በ
ሥራ ዓለም ተሰማርተውና እራሳቸውን
ችለው በማየቴም እደሰታለሁ አሁንም
ወደዚያ ሊደርሱ ይገባቸዋል ብዬ የምረ
ዳቸውና በሥሬ ያሉት ፦

የኋላሸት ከበደ የ11ኛ ክፍል ተማሪ
ፍስሐ ደርበው የ8ኛ ክፍል ተማሪ
ነጋሽ ከበደ የ3ኛ ክፍል ተማሪ
ፍቃዱ ይፍሩ የ4ኛ ክፍል ተማሪ
ክብነሽ መለሰ የ5ኛ ክፍል ተማሪ
ጥሩነሽ በቀለ ተማሪ
አሚናት አህመድ ተማሪ
ናቸው ሲሉ አስተዋውቀውናል ። በዚ
ህ ልናስተውለው የሚገባ ሰው ባለው
ቅንነትና ፍቃደኝነት ከተነሳ ብዙ ነገሮ
ችን ሊያበረክት እንደሚችል ነው ።

እግረመንገዳችንን ከነዚሁ መካከል
አንዳንዶቹን ጠይቀን የሰጡንን አስተ
ያየት እንመልከት በመጀመሪያም ፍስ
ሐ ደርበውን አነጋግረነው ለ፱ ዓመ
ታት በእሳቸው እየተረዳ መኖሩን አስቀ
ድሞ ገልጾልናል ። ምክንያቱም በወሎ
ክ/ሀገር ልዩ ስሙ ጥንጂት አምባ ጊዮር
ጊስ በተባለው ስፍራ ተወለደ ። ለ፲ ዓ
መት ያህል እንደቆየ በወሎ ክ/ሀገር ተ
ደም ብሎ በደረሰው የተፈጥሮ ችግር
ምክንያት ከነቤተሰቦቹ ተሰደደ ዘመዶ
ቹ ወደ ሌላ ሲሄዱ እሱ ግን አዲስ አበባ
መጥቶ ጐፋ ገብርኤል አካባቢ ከነአባ
ቱ አርፎ ሳለ በአንዳንድ ሁኔታው ሲያ
ዩት ያዘኑና የኝህን ሴት ደግነት ያውቁ
የነበር አንዲት ሴት ወስደው ከነአባቱ
እንዲተዋወቁ ያደርጉአቸዋል ። ከዚያ
በኋላ አንዲት ሌላ ሴት ልጄን እኔ
አሳድጋለሁ በማለት ከወሰደችው በ
ኋላ እንኳን አሳድጋ ልታስተምረው ይ
ቅርና በሀገሩ ከደረሰበት የበለጠ ችግር
እንዲደርስበት ለማድረግ የወሰደችው
ይመስል ከብት ጠባቂ ታደርገውና ይባ
ስ ብላ ከሰብአዊ ርህራሄ ውጪ ሰውነቱ
እስኪቆስል ትገርፈዋለች ያን ጊዜ የ፲
ዓመት ልጅ መሆኑን ገልጾልናል በዚህ
ጊዜ ውስጥ አባትየው ሊጠይቁት ቢሄ
ዱ እንዲህ ሆኖ በማየታቸው አዝነውና
አልቅሰው እኚሁ ሴትጋ ይወስዱታል
እሳቸውም አይተው በማዘን እርሱን ይ
ተውት እኔ አሳድገዋለሁ በማለት ለአባ
ትየው ደግሞ በሬና የሚያስፈልጋቸው
ን ገዝተው ወደሀገራቸው እንዲመለሱ
ይረዱና ይልኩአቸዋል ። ከዚያ በኋላ ይ
ኸንን ልጅ እራሳቸው ፊደል አስቆጥረ
ው በመጣ በ9 ዓመቱ የ8ኛ ክፍል ተማ
ሪ እስከሚሆን እንዳደረሱትና አሁንም
በመማር ላይ መሆኑን ገልጾልናል ።
እኛም ሁላችን የእኒህን ሴት አርአያ እ
ንከተል ።

## ደብዳቤዎች

ከገጽ ፲፮ የዞረ

ሰዓት ድምር ፲፰ ሰዓት ልዩ ልዩ መከራ
የተቀበለ ለመሆኑ የዚህ ምሳሌ ነው ይ
ላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ መንገደ ሰማይ
የሚለው መጽሐፍ መሥዋዕተ ኦሪት ለ
መሥዋዕተ ሐዲስ ምሳሌው እንደሆነ
በሚለው ርእስ ፣ በገጽ ፹፯ ላይ ። የበላ
ችሁትና የወጣችሁት ከአፋችሁ ጠፍቶ
ምሬት ሲሰማው ፲፰ ሰዓት ከምግብ ተ
ከልክላችሁ በመጾም ቁረቡ በማለት ሲ
ገልጽ ፣ ምሳሌውም እመቤታችን ድን
ግል ማርያም ጌታን በ፲፰ ዓመቷ ጸንሳ
ዋለችና ስለዚህ ነው ይላል ። ኸረ ለመ
ሆኑ የትኛው ነው ትክክለኛው ?
ወኪል ፖስታ ቤት ሠራተኛ
መምሬ ተስፋዬ ደረቱ

መምሬ ተስፋዬ ደረቱ ስለ አቀረቡአ
ቸው ጥያቄዎች እናመሰግንዎታለን ።
መንፈሳውያን መጽሔቶችንና መጻሕ
ፍትን አዘውትረው መከታተልዎም እ
ጅግ አስደስቶናል ።

መጽሐፎቻቸውን አንብበው የጠቀ
ሱአቸው ሊቃውንት ሁሉም በሕይወተ
ሥጋ ይገኛሉ ። ስለዚህ ራሳቸው መልስ
እንዲሰጡባቸው ጥያቄዎቹን በሙሉ አ
ውጥተናቸዋል ።

* *

ለትንሣኤ መጽሔት
አዲስ አበባ

የእመቤታችን ቅድስት ድንግል ማር
ያም እናት ቅድስት ሐና ጽላት ተቀርጾ
ላት ቤተ ክርስቲያን ታንጾላት ይገኛል
ወር በገባ በየ፲፩ኛው ቀንም የዕረፍትዋ
መታሰቢያ ይደረጋል ፣ የእመቤታችን
አባት ቅዱስ እያቄምስ ታቦት ያልተቀ
ረጸለት ቤተ ክርስቲያን ያልታነጸለት
ስለምን ይሆን ? ጽላት የተቀረጸለትና
ቤተ ክርስቲያን የታነጸለትም ከሆነ
በየትኛው ክፍለ ሀገር እንደሚገኝ አ
ስረዳን ።
ጠያቂዎች ፩ኛ/ ወ/ሮ አስካለ ቱላሞ
ከ14 ቀ.22

ተከታዩን በገጽ ፲ ይመልከቱ



# ኢ.ኦ.ተ.ሐ.ድ

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፣ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፣ መንፈሳዊ ዘመናዊ መዝሙሮችን ፣ ትምህርቶችንና ኖል ማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቴፕ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላናረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ በማስከፈል ይሰጣል ።

ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ሐዋርያዊ ድርጅት
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት

ስልክ ቍ. 116616
የመል. ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ

www.ethiopianorthodox.org